ትማሪ
TIMMAR

FAWE
Ethiopia Chapter

ቅጽ 23



2017

ታህሳስ 2017

Our Vision

An equitable and inclusive Ethiopia where all girls and women thrive.

Our Mission

To promot gender-responsive education in Ethiopia, ensuring equal oportunities for all girls and women to thrive and excel in all areas of life.

Strategic Objectives

01 Increase enrollment, retention, and completion rates for girls and young women at different levels of the education.

02 Promote gender-responsive pedagogy and ensure inclusive, empowering education including on digital literacy and life skills.

03 Equip girls and young women with leadership skills, confidence, life skills and economic opportunities.

04 To mobilize communities and stakeholders in Ethiopia to support girls' education and address systemic barriers.

Values

FAWE Ethiopia Chapter values Impact-Oriented, Innovation, Involvement, Inclusivity and Integrity. We are passionate about results, and are dedicated in everything we do.

Governance

- General assembly
- Board

The board has 7 members 100% female.

Management committee

The management committee has 4 members with 75% female

ማውጫ

01 የፋዌ-ኢትዮጵያ ቻፕተር አ.ኤ.አ የ2024 ዓ.ም. ዓመታዊ የሥራ ክንውን

02 የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ምእራፍ ፪

06 ብሬክ ፍሪ ፕሮግራም

08 ሜክ ዊይ ፕሮጀክት

10 ቱሰሜ ፕሮጀክት

11 የኢግናይት ፕሮጀክት

11 የትማር እንግዳ፡- እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)

14 የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ

ሴት ልጆችን ማብቃት ፣ ሀገራትን መለወጥ፡ - የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዋና ሥራ አስፈፃሚ መልእክት



እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ፣ የእድገት እና የተፅዕኖ ዓመት ሆኖ ባለፈው የ2016 ዓ.ም. የቻፕተራችን አፈፃፀም ላይ በመመሰረት፣ ይህንመልእክትበፋዌ ኢትዮጵያ ዓመታዊ መጽሄት ላይ የማጋራት እድል በማግኘቴ ከፍተኛ ክብር ይሰማኛል።የልጃገረዶች የትምህርት ተሳትፎ በመላው ኢትዮጵያ እንዲያድግ ያለን ቁርጠኛ አቋም የተመሰረተው፣ አጋሮቻችን፣ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና የህብረተሰብ ክፍሎች በቻፕተራችን ላይ ባሳደሩት ጠንካራ እምነት ላይ ነው። በመሆኑም፣ እነዚህ አጋሮቻችን በጣሉብንን እምነት ሰንቀንና በጠንካራ የኃላፊነት ስሜት ታጅበን፣ ልጃገረዶች በቀጣይ የህይወት ጉዞቸው ውስጥ የሚያጋጥማቸውን ፈተናዎች የሚቋቋሙ፣ የተለያዩ እድሎቿን ባግባቡ የሚጠቀሙና ቀጣይ ህይወታቸውን ባግባቡ የሚመሩ እንዲሆኑ በትጋት እየሠራን እንገኛለን።

ያለፈው 2016 ዓ.ም. የጥንካሬ እና የለውጥ ጉዟችን መገለጫ ሆኖ አልፏል። ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ተሟጋችነቱን ይበልጥ ያጎሉ፣ አጋርነቱን ያጠናከሩ፤ የመገለል አደጋ ውስጥ ያሉ ልጃገረዶችን ለመደገፍ የሚያስችሉ አዳዲስ ፕሮግራሞችን ቀርፆ ሥራ ላይ አውሏል። በዚህም መሰረት፣ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነቶችን በሚፈቱ ተነሳሽነቶች፣ ለአብነትም በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና እና በሂሳብ ላይ ያተኮረ የSTEM ፕሮግራምን እናበቴክኒክና ሙያ ትምህርት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የሚያሳድጉ ተግባራትን በመከወን፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣት ልጃገረዶች የእውቀት እና የክህሎት ባለቤት እንዲሆኑ እና የአመራር ተሳትፏቸው እንዲጎለብት እናኢኮኖሚያዊ ነፃነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ እየሰራይገኛል።

በሀገራቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የለውጥ አካል ከመሆን የሚያግዷቸውን መሰናክሎችን በመቋቋም ለስኬት የበቁ ልጃገረዶች አነቃቂ ታሪኮች ማጋራትና እነሱንም ምሳሌ ማድረግ ፣ ለአብነት ከሚጠቀሱ ፋዌ ኢትዮጵያ በቁርጠኝነት እያከናወናቸው ተግባሮቹ መካከልናቸው። በስኮላርሺፕ ፣ በአማካሪነት ፣ ወይም በፖሊሲ ጉዳዮች ዙሪያ በሚያከናውናቸው የጉትጎታና የቅስቀሳስራዎቹ አማካይነት ፣ ለሴቶች እና ለልጃገረዶች እኩል እድል እንዲያገኙና ለውጤት እንዲበቁ የማድረግ ተልዕኮውን እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ የሚቀጥል መሆኑን እያረጋገጥሁ ፤ ቻፕተሩከ መማር ማስተማር የክፍል ውስጥ መስተጋብር ባሻገር ፣ የፆታእኩልነት ፣ አካታችነት እና የዕድሜልከ ትምህርት በማህበረሰቡ ዘንድ ባህል እንዲሆኑም ያላሰለሰጥረቱን እንደማያቋርጥ ለመግለጽ እወዳለሁ።

በዚህዓመት በእቅዳችን መሰረት ፣ በተለያዩ ፕሮግራሞቻችን አማካይነት የምናገለግላቸውን ወጣት ሴቶች ደህንነት ለመጠበቅ እና ለመከላከል ያለንን ቁርጠኝነት የማረጋገጥ ሥራ የምንሰራ ሲሆን ፤ ከዚህ አኳያ፣ ፖሊሲዎችን በማጠናከር እና አቅምን በማሳደግ ልጃገረዶች ከአድልዎ እና ከጥቃት ነፃ ሆነው የሚያድጉባቸው ፣ ደህንነታቸውም የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎች እንዲፈጠሩም የበኩላችንን ጥረት ለማድረግ ቁርጠኞች መሆናችንን ስገልጽ የሚሰማኝ ክብር ታላቅ ነው።

ባለፉት ዓመታት የስኬት ጉዞው መሰረት ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ በትምህርት ፖሊሲዎች ላይ ስርዓታዊ ለውጦች እንዲኖሩ፣ ለልጃገረዶች ትምህርት የሚውለው መዋዕለንዋይ ይበልጥ እንዲጨምር፣ የመማር እድሎችን ከማስፋት አንፃር የቴክኖሎጂ አማራጮች እንዲሰፉ የማድረግ ጥረቱም እንዲሁ ቀጣይ የስራና የጉትጎታ አቅጣጫዎቹ ናቸው። በዚህ ወሳኝ ሀገር ተኮር ተልዕኮ ውስጥ፣ የመንግስት አካላት፣የልማት አጋሮቻችን እና የተለያዩ የማህበረሰቦች ክፍሎች እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ ከጎናችን እንዲቆሙ በቻፕተራችን ስም እየጠየኩ፣ ሴትልጆችን ማብቃት የሞራል ሃላፊነት መወጣት ላይብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ለኢትዮጵያ ዘላቂልማት በጣም ወሳኝነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተግባር መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እጠቁማለሁ።

ያለፍርሃት ቀጣዩን የስኬት ጉዞዋን ለምታልም እያንዳንዷ ልጃገረድ፣ የውስጡን አቅም አሟጦ ለመጠቀም ለሚታትር እያንዳንዱ የትምህርት ሰው፣ ለወጣት ሴቶች የወደፊት እጣፈንታ መሻሻል በድጋፉ አለኝታ ለሆነን እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ሁሉ፣ በዚህ የፋዌ ኢትዮጵያ ጉዞ ውስጥ አካልሆናችሁ ለምታደርጉት ተሳትፎ ሁሉ በቻፕተራችን ስም ያለኝን አክብሮት እና ምስጋና እገልፃለሁ። አንድላይ ሆነን፣ እያንዳንዷ ልጃገረድ የራሷን ታሪክ የምትሠራበትን ሀገር እየገነባን መሆኑን አንርሳ።

ሰላማዊት አድማሱ

የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዋና ሥራ አስፈፃሚ

የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር

2016 / 17 ዓመታዊ የሥራ ክንውን

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች መድረክ (FAWE) አንደኛው አባል እንደመሆኑ፣ በመድረኩ የመቋቋሚያ ተልእኮ፣ ዓላማና ስልታዊ ግቦች መሰረት፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚቀረፁ ፖሊሲዎች ከሥርዓተ-ፆታ አኳያ የተቃኙ እንዲሆኑ፣ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጡ የመማሪያ ማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲተገበሩ፣ እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደቱ አካታችነቱና ፍትሃዊነቱ፣ እንዲሁም ምቹነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ተገቢውን የግንዛቤ ሥራ መሥራት ላይ ባተኮሩ የተለያዩ ተግባራት ዙሪያ ዓላማውን ዳር የሚያደርሱ ተግባራትን እያከናወነ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም መሰረት፣ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ፣ በ 2016 / 2017 ዓ.ም ፋዌ-ኢትዮጵያ በቀደሙት ዓመታት የተጀመሩ ፕሮግራሞቹን በማስቀጠል እና አዲስ የተጀመሩ ፕሮግራሞቹን እና ፕሮጀክቶቹን በመተግበር ረገድ ትልቅ እመርታ አሳይቷል። በዓመቱ ያከናወናቸው እነዚሁ ተግባራቱ፣ ቀደም ብሎ የጀመራቸውንም ሆነ በአዲስነትም መተግበር የጀመራቸውን ፕሮግራሞቹንም ሆነ ፕሮጀክቶቹን ይበልጥ በውጤታማነት ዳር ለማድረስ የረዱ ከመሆናቸውም በላይ፣ ለሁሉም የሃገራችን ዜጎች ትምህርትን በፍትሃዊነት በማድረስ በኩል ያለውን ተነሳሽነት ይበልጥ እንዲያጠናክር የረዱ ናቸው።

የተገባደደው ዓመት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ሀብት በማሰባሰብ ረገድ ከፍተኛ እመርታ ያሳየበት እና ተፅእኖውን ምይበልጥ ያሰፋበት፣ ብዙ ተጠቃሚዎችን ምተደራሽ ያደረገበት ዓመት ሆኖ አልፏል። በዚህም መሰረት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ በስርዓተ ፆታ መሪ ድርጅትነቱ ባገኘው እውቅና መነሻነት፣ በተግባራቱም

የመጀመሪያ ምእራፍ አፈፃፀም በነበረው አመርቂ ውጤት መሰረት፣ የማስተርካር ድፋውንዴሽን የምዕራፍ ፪ ፕሮግራምን፣ እንዲሁም በሴቭ ዘቸልድረን የሚመራውን እና በአጋርነት ተነሳሽነት እየተተገበረ ያለውን MYRP የምእራፍ ፪ ፕሮግራምን (Multi-Year Resilience Program / MYRP II) በተሳካ ሁኔታ አስጀምሯል። ከእነዚህ በተጨማሪም ፣ ዓመቱ በIDRC-KIX የሚደገፈው TUSEME እና በ UAF-Africa የሚደገፈው IGNITE የተሰኙ ፕሮጀክቶች በፋዌ ኢትዮጵያ በኩል መተገብር የጀመሩበት ዓመትም ነበር። የእነዚህ ሁለት ፕሮጀክቶች በፋዌ ኢትዮጵያ እንዲተገበሩ መደረጋቸው፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ለስርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ ለሆነ የትምህርት አካባቢዎች መፈጠር ያለውን ቁርጠኝነት የበለጠ እንዲያጎለብት የሚያደርጉ ናቸው።

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር የነበሩትን የአጋርነት ግንኙነቶችን ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መልኩ በማጠናከርና አዳዲስ ስትራቴጂካዊ ግንኙነቶችንም እውን በማድረግ እና የተለያዩ የገንዘብ የድጋፍ ምንጮችን በማስፋት፣ የተለያዩ መዋቅራዊ ለውጥ ሊያስከትሉ የሚችሉ እና ልጆችም ሆኑ በወጣትነት እድሜ ውስጥ ያሉ ሁሉያለ ሥርዓተ-ፆታ ልዩነት የመማር፣ የማደግ እና በስኬትም ህይወታቸውን የመምራት እድል በሚሰጥ ደጋፊ እና አካታች የትምህርት ከባቢ ውስጥ እንዲያልፉ የሚያደርጉ ተግባራትን እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ በዓመቱ ሲተገብር ቆይቷል። የእነዚህ ተግባራቱ የዓመቱ አፈፃፀም እንደሚከተለው በየፕሮግራሞቹ ቀርቧል።



የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ምእራፍ ፪

የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የምዕራፍ ፪ ፕሮግራም፣ የሰባት ዓመት ቆይታ ያለውና ከ.ኤ.አ.ከ2024 እስከ 2030 ዓ.ም. ድረስ የሚተገበር ፕሮግራም ሲሆን፣ ወጣቶችን በተለይም የሴት ልጆችን በራስ የመተማመን መንፈስን ማዳበር ላይ በማተኮር እና ሁሉን አቀፍ ተግባራትን በመተግበር፣ ከአህዚሀሁ የህብረተሰቡ ክፍሎች የከፍተኛ ትምህርት ዕድልን በማመቻቸት እና በሂደትም ወደሥራ ዓለም የሚሸጋገሩበትን ሂደት ማጎልበት ላይ ያለመ ነው። ፕሮግራሙ፣ አራት ዋና ዋና ዓላማዎች ያሉት ሲሆን፣ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

ቁልፍ ተግባራት እና ስኬቶች

- በተለያዩ ምክንያቶች ለመገለል ከተጋለጡ የህብረተሰቡ ክፍሎች ለተውጣጡ 800 ያህል ወጣቶች ፣ ጠቃሚ የሆኑ የገበያ ክህሎቶችን እና የሥራ ፈጠራ ልምዶችን እንዲያዳብሩ የሚያስችሉ እድሎችን ማሳደግ፣
- ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የሆነ ሥርዓተ-ትምህርት እና ከዚሁ ጋር የተገናዘቡ የመማር ማስተማር ሞዴሎች ከሥራ ገበያ ፍላጎቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ የሚተገበሩበት ሁኔታ ይበልጥ እንዲሻሻል ጥረት ማድረግ፣
- በወጣቶች በሚመሩና በውጤታማነት ላይ ያሉ የንግድ ሥራዎችን፣ በሥራ እድል ፈጠራ ላይ፣ በሥራ ምደባ እና በኢንዱስትሪ ትስስር ረገድ ድጋፍ ማድረግ፣
- ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የሆኑ ፕሮግራሞች ፣ ፖሊሲዎች እና የአሠራር መመሪያዎች ከአጋር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፣ ከህብረተሰቡ የተለያዩ አካላት ፣ ከወላጆች እና ከተማሪዎች ጋር በሚኖር ትብብር መሰረት ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣



ፋዌ ኢትዮጵያ፣ እ.ኤ.አ. ነሐሴ 29 ቀን 2024 ዓ.ም. ይህንን የማስተርካርድ ፋውንዴሽንን የምዕራፍ ፪ ፕሮግራምን ፣ ከ2024-2028 ዓ.ም. ድረስ ሥራ ላይ ከሚውለው ስትራቴጂያዊ እቅድ ጋር አዲስ አበባ በሚገኘው የሀያሌ ግራንድ ሆቴል በይፋ አስጀምሯል። በዚሁ የፕሮግራም ማስጀመሪያ ሥነሥርዓት ላይ፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ከሠራተኛና ክህሎት ሚኒስቴር የተወከሉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ የተለያዩ የክልል ቢሮዎች ተወካዮች፣ የፕሮግራሙ አጋር የሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ የተለያዩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅቶች፣ አጋር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የፋዌ ኢትዮጵያ የየክልሎ ቻፕተሮች ተወካዮች፣ የፋዌ ኢትዮጵያ የቦርድ አባላት እና በፋዌ ኢትዮጵያ የተለያዩ ፕሮግራሞቹ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ የቀድሞ ተማሪዎች፣ በአጠቃላይም 117(ሴ=53) ተሳታፊዎች ታድመዋል።

ከፋዌ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የምዕራፍ ፪ ፕሮግራም ይፋዊ የፕሮግራም ማስጀመሪያ የመክፈቻ ሥነሥርዓት አስቀድሞ፣ በፕሮግራሙ አተገባባር ወቅት ቁልፍ ሚና ካላቸው የመንግስት ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትብብር ማሳደግ ላይ ያተኮረ የሥራ ጉብኝት፣ በሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እና በትምህርት ሚኒስቴር ተካሂዷል። በጉብኝቱ ወቅትም፣ የፕሮግራሙን ዓላማዎች ቅድሚያ ከተሰጣቸው ሀገራዊ የትምህርት እና የክህሎት ልማት የትኩረት ጉዳዮች ጋር ማጣጣም ላይ ያተኮረ ውይይት የተካሄደ ሲሆን፣ በየሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቹ በተካሄዱት ውይይቶች ላይም፣ የፋዌ አፍሪካ ዋናው ጽ/ቤት ዳይሬክተር፣ የፋዌ ኢትዮጵያ ሥራአስፈፃሚ፣ የትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ፣ የሠራተኛና ክህሎት ሚኒስቴር ሃላፊዎች እና የአጋር ድርጅቶች ተወካዮች እና ሌሎች ከፍተኛ ልዑካን ተሳታፊዎች ነበሩ።



ከዚሁ የፋዌ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የምእራፍ ፪ ፕሮግራም ጅማሮ ጋር በተያያዘ፣ የፕሮግራሙ ትግበራ የቅድመ ዝግጅት አንድአካል የሆነውና በቀድሞው የማስተርካርድ የስኮላርሽፕ ፕሮግራም የምእራፍ ፩ ተጠቃሚ የነበሩ ተማሪዎችን ያሳተፈ ስብሰባ ነሐሴ 27 ቀን 2024 ዓ.ም. ተካሂዷል። ከባህር ዳር፣ ከአዲስ አበባ፣ ከአዳማ እና ከሀዋሳ የተውጣጡ 11 ተማሪዎችን በማሰባሰብ የተካሄደው ይህ ስብሰባ፣ እነዚህ የቀድሞ ተማሪዎች ልምድ እንዲለዋወጡ ከማስቻሉም በላይ፣ በምእራፍ ፩ ትግበራ ወቅት ሊወሰዱ የሚችሉ ተሞክሮዎችን በተመለከተ የሃሳብ ልውውጥ የተደረገበት ነበር።

ከፕሮግራም ማስጀመሪያ ሥነሥርዓት በመቀጠል ከተከናወኑ ተግባራት ውስጥ ሌላው፣ አዲስ አበባ በሚገኘው የጄኔራል ዊንጌት ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ በመገኘት የተካሄደው የልምድ ልውውጥ እና የአጋርነት ግንባታ ጉብኝት ነበር። ጉብኝቱ፣ ከኡጋንዳ፣ ከላይቤሪያ፣ ከሩዋንዳ፣ ከዛምቢያእና ከታንዛኒያ የተወከሉ የፋዌ ብሄራዊ ቻፕተሮች ተወካዮችን፣ የፋዌ አፍሪካ ዳይሬክተርን እና የስድስት አጋር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ዲኖችን፣ የሚመለከታቸውን የፋዌ ኢትዮጵያ አባላትን፣ በአጠቃላይም 22 ልዑካንን ያሳተፈነበር።





የፋዌ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የምእራፍ ፪ ፕሮግራም ጅማሮ እንደአንዱተግባር ሆኖ የሚቆጠረው፣ ፕሮግራሙ ከሚተገበርባቸው ክልሎች የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበትና በተከታታይነት የተካሄዱት ፕሮግራሙን የማስተዋወቂያ ዐውደጥናቶች ናቸው። በእነዚህ ዐውደጥናቶች ላይ፣ ከክልል መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ ከማህበረሰብ አቀፍ ማህበራት፣ በፋዌ ኢትዮጵያ የስኮላርሽፕ ፕሮግራሞች ውስጥ ባለፉ የቀድሞ ተማሪዎች ውስጥ ባለፉ የቀድሞ ተማሪዎች ከተቋቋሙ ማኅበራት እና ከተለያዩ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት የተውጣጡ 189 ተሳታፊዎች (ከእነዚህ ውስጥ 30 ሴቶች ነበሩ) ተሳትፈዋል። እነዚህ ዐውደ ጥናቶች፣ የምእራፍ ፪ ፕሮግራም ዓላማዎችን፣ አጠቃላይ ግቦችን እና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ የህሳብ ልውውጥ የተካሄደባቸው እና በፕሮግራሙ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ እነዚህ ባለድርሻ አካላት በባለቤትነት መንፈስ ስለሚኖራቸው አስተዋፅኦ ግንዛቤ የተጨበጠባቸውም ነበሩ።

ፍትሃዊና ግልፅነት ያለው የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች የምልመላ ሂደት እንዲኖር ለማስቻል፣ ክልላዊና አካባቢያዊ የአስመራጭ ኮሚቴ ስብሰባዎች ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ክልሎች ተካሂደዋል። በየክልልቹ የተካሄዱ የየኮሚቴዎቹ ስብሰባዎች፣ የክልል መንግሥታዊ መሥሪያቤቶችን፣ የማህበረሰብ አቀፍ ማህበራትን፣ በፋዌ ኢትዮጵያ ስኮላርሽፕ ፕሮግራሞች ውስጥ ባለፉ የቀድሞ ተማሪዎች የተቋቋሙ ማህበራትን፣ የቴክኒክና ሙያትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን እና የአካል ጉዳተኛ ማህበራትን ተወካዮች ያሳተፉ ነበሩ።

የፋዌ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የምእራፍ ፪ ፕሮግራም ባግባቡ እንዲተገበር የሚያስችል የፕሮጀክት ትግበራ የአጋርነት ስምምነት፣ በፋዌ ኢትዮጵያ ከአማራ፣ ከሲዳማ እና ከኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተውጣጡ የተለያዩ የመንግስት መሥሪያቤቶች ኃላፊዎች ጋር ተካሂዷል። እነዚህ የአጋርነት ስምምነቶች፣ ለሰባት ዓመታት (2024-2030) የሚቆየውን የዚህን ፕሮግራም አፈፃፀም ሂደት በስኬት በማጠናቀቅ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚኖራቸው ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ይህንን ፕሮግራም የተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደር ከሚገኙና በአጋርነት ከተመረጡ 6 የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች ጋር ተፈራርሟል።

በፋዌ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የምእራፍ ፪ ፕሮግራም ትግበራ ውስጥ በአጋርነት እንዲሳተፉ የተመረጡ፣ 6 የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እና ኮሌጆች፣ ከፕሮግራሙ ትግበራ አኳያ ያላቸውን ዝግጁነት የተመለከተ ተቋም ተኮር ምዘና እንዲካሄድ ተደርጓል። ይህ የተቋማትን የአቅም ሁኔታ በተመለከተ የተካሄደው ምዘና፣ ዳሰሳ ተኮር በሆነ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ሲሆን፣ የተቋማቱን ወቅታዊ ደረጃ ለመገምገም እና በቀጣይነትም ተቋማቱ በፕሮግራሙ የትግበራ ሂደት ውስጥ የሚያሳዩትን ተቋማዊለውጥ እና እድገት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመከታተል እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነው።



እፁብድንቅ አስቻለው ይተዋወቁ

በፋዌ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የምእራፍ ፪ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችሉ እድሎች በስፋት ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ስለሚያስችሉ ሁኔታዎች እና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካያም ተሳታፊ ሆነው ለሚመረጡ አካላት ስለሚሰጡ ድጋፎች ዝርዝር መረጃዎች በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል። በዚህም መሰረት፣ በማስተርካርድ ፋውንዴሽን የምዕራፍሁለት ፕሮግራም አማካይነት አዳማ፣ ሀዋሳ፣ አዲስ አበባ እና ባህር ዳር ባሉ ስድስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ የሚሳተፉ 192 ተማሪዎች ሊመረጡ ችለዋል። ከተመረጡት ተሳታፊዎች መካከልም፣156ቱ (81%) ሴቶች፣16ቱ (8%) አካልጉዳተኞች ሲሆኑ፣ 13ቱ (7%) ደግሞ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ክልሎች ውስጥ በሚገኙ ከተሞች ውስጥ የሃገር ውስጥ ተፈናቃይ የሆኑ ግለሰቦች ናቸው።

በፕሮግራሙ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች ምርጫ ከተካሄደ በኋላ፣ ለተሳታፊ ሰልጣኝ ተማሪዎች የተለያዩ ድጋፎች ተደርገዋል። በዚህም መሰረት፣ በአዳማ ለ33 (25 ሴት፣8 ወንድ)፣ በሐዋሳ ለ13፣ በአዲስ አበባ ለ6 ተማሪዎች፣ በባህርዳር ለ15 እና ለ3 አካልጉዳተኛ ተማሪዎች (2 ሴት፣1 ወንድ) የመኖሪያ ቤት ድጋፍ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም፣ በስድስቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ ለሥልጠና የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ ሥልጠናቸውን በተሳካ ሁኔታ መከታተል እንዲችሉ፣ ዩኒፎርም ተሰጥቷቸዋል፣ የትራንስፖርት ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፣ የአበልክፍያ ተፈፅሞላቸዋል፤ እንዲሁም የምዝገባ ክፍያ ወጪያቸው ተሸፍኗል።

በፕሮግራሙ እንዲሳተፉ ለተመረጡ ሰልጣኝ ተማሪዎች፣ በተመደቡባቸው ተቋማት ስለሚከታተሏቸው የስልጠና ኮርሶችእና ከስልጠና መጠናቀቅ በኋላም በወሰዷቸው ስልጠናዎች አማካይነት በሙያቸው አማካይነት በቀጣይ በሚያጋጥሟቸው ህይወት ለዋጭ እድሎች ላይ ያተኮረ የገለባ ፕሮግራም ተካሂዷል። ከዚህ ገለባ በመቀጠልም፣ በፕሮግራሙ ውስጥ እንዲሳተፉ የተመረጡ ተማሪዎች በፀፉ የፕሮግራሙ አካል መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሥነሰርዓት ወላጆቻቸው በተገኙበት ተካሂዷል።

ከፕሮግራሙ ትግበራ ጋር በተያያዘ፣ አቅምግንባታ ላይ ያተኮረ ተግባር ተከናውኗል። በዚህም መሰረት፣ ከጤና፣ ከደህንነት እና ከሰብአዊ መብቶች እና ከመሳሰሉ ጉዳዮች ጥበቃ ጋር እና ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን እና አሉታዊ ልምምዶችን ከመከላከል ጋር የተያያዘ የግንዛቤ ማስጨባጫ ስልጠና፣ ለፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ሠራተኞች ከታህሳስ 23 እስከ 24 ቀን2024 ድረስ አርባምንጭ በሚገኘው የሃይሌሪዞርት ሆቴል ተሰጥቷል። የልምድ ልውውጥን፣ የቡድን ውይይቶችን እና ተግባራዊ ልምምዶችን ባካተተው በዚህ የአቅም ግንባታ ስልጠና ላይ፣ አስራ ሰባት ተሳታፊዎች (11 ሴቶች ፣ 6 ወንዶች) ታዳሚዎች ነበሩ። በመቀጠልም፣ በዚሁ የአቅም ግንባታ ስልጠና ማጠናቀቂያ ላይ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር በ2024 ዓ.ም ባከናወናቸው ፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም ሂደት ላይ የተመዘገቡ ስኬቶችን፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን እና በልምድነት ሊወሰዱ የሚችሉ ጉዳዮችን የተመለከቱ የተለያዩ ገለፃዎች ተሰጥተው ውይይት ተካሂዶባቸዋል። እንዲሁም፣ የቻፕተሩ የ2025 ዓ.ም. ስትራቴጂካዊ የሥራ እቅዶችን የተመለከተ ገለፃም ተደርጓል።

በሀዋሳ ከተማ፣ ከእናቷ እና ታናሽ ወንድሟ ጋር የምትኖረው የ20 አመት ወጣቷ እፁብድንቅ አስቻለው፣ በወጣትነት ህይወቷ በትልቅ ፈተና ውስጥ ያለፈች ነች። ገና በስምንት ዓመቷ ነበር፣ በከባድ ህመም ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሰባት። በተጨማሪም፣ የወላጆቿ ጋብቻ በፍቺ መጠናቀቁ፣ ቤተሰብ የማስተዳደር ጫናው እንዳለ በእናቷ ትከሻ ላይ ብቻ እንዲወድቅ አደረገ። እናቷ፣ እንዳጋጣሚ ሆኖ ቋሚ ገቢ የሌላቸው ናቸውና፣ ለቤተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላት የማያቋርጥ ትግል የማድረግ ግዴታ ነበረባቸው። በዚህ ሁሉ ተግዳሮት ውስጥ ግን፣ እፁብድንቅ በ2016 ዓ.ም. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ማጠናቀቅ ያስቻላትን የማጠናቀቂያ ፈተና በመውሰድ፣ ለሬሜዲያል ትምህርት የሚያበቃትን ውጤት ማስመዝገብ ቻለች። ሆኖም፣ ይህን የሬሜዲያል ትምህርት በመከታተል ዩኒቨርስቲ የመግባት ምኞቷን እውን የማድረግ ፍላጎት ቢኖራትም፣ የቤተሰቧ የአቅም ውስንነት በዲላ ዩኒቨርሲቲ የተመደበችበትን ይህን የሬሜዲያል ትምህርት እንዳትከታተል እንቅፋት ሆነባት። እፁብድንቅ ትምህርቷን ለመቀጠል ባላት ከፍተኛ ፍላጎት ላይ የተደቀነባት ይህ መሰናክል፣ ስሜቷን ክፉኛ ጎድቶታል፤ ተስፋም እንድትቆርጥ አድርጓታል።

በዚህ ፈታኝ ወቅት ግን፣ እፁብድንቅ በፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር በኩል ስለሚተገበረው የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ ፕሮግራም ሁለተኛው ምእራፍ ተስፋዋን የሚያለመልም መረጃ ሰማች። ባገኘችው መረጃም፣ ትምህርቷን ለመቀጠል የሚያስችላት እድል እንዳላት ተሰማት፤ ከረጅም ጊዜ የመቆዘም ጊዜ በኋላም የደስታ ስሜት በውስጧ ፈነጠቀ። እናም ተስፋዋን ሰንቃ በፕሮግራሙ ውስጥ እንድትታቀፍ የሚያስችላትን ማመልከቻ የፕሮግራሙን ተሳታፊዎች ለሚመለምለው ኮሚቴ አስገባች። ሆኖም፣ መጀመሪያ ላይ ተስፋ እንዳደረገችው በፕሮግራሙ ውስጥ የመካተት እድል ሳታገኝ ቀረች። ባለመመረጧ ያደረባትን ቅሬታ እያብሰለሰለች፣ ያለችበትን ሁኔታ የፕሮግራሙ መልማይ ኮሚቴ አባላት እንዲረዱላት ማድረግ እንዳለባት ራሷን አሳመነች። በመሆኑም፣ ለመራጭ ኮሚቴው ያለችበትን ሁኔታ በቃል አስረዳች። ኮሚቴውም ባቀረበችው አቤቱታ ላይ ጥልቅ ውይይት ካደረገ እና ጉዳዩን በጥሞና ከመረመረ በኋላ፣ እፁብድንቅ ያለችበትን ሁኔታ እና ያላትንም እምቅ አቅም በመገንዘብ፣ በፕሮግራሙ ውስጥእንድትካተት ወሰነ። ይህ ውሳኔ፣ እፁብድንቅ ህልሟን እውን እንድታደርግ መሰረት የጣለላት ህይወት ለዋጭ ክስተት ሆነ። በመሆኑም፣ እፁብድንቅ በፕሮግራሙ እንድትካተት የሚያስችላትን እድል አገኘች።

እፁብድንቅ፣ በስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ ከተዘረጉ የስልጠና መርሃግብሮች መካከል አንዱ በሆነው በፋሽንዲዛይን የስልጠና መስክ በሀዋሳ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ተመዝግባ፣ ታላቁን የጥንካሬ ጉዞዋን አንድ ብላ ጀመረች። የሥዕል ልዩ ተሰጥኦዋ እና የፋሽን ዲዛይን ለማጥናት ያላት ፍላጎቷ አንድ ላይ ሆነው ህልሟን ለማሳካት እንደረደሯት። በተጨማሪም፣ እፁብድንቅ ጥረቷ ዳር እንዲደርስ እና ፍላጎቷ እንዲሰምር አብረዋት ከሚሰለጥኑ ወጣቶች ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖራት እንደሚገባ በመረዳቷም፣ ለነበራት ቅርርብ እና ለፈጠረችው ግንኙነት ከፍተኛ ዋጋ ሰጥታ ተንቀሳቅሳለች።

እፁብድንቅ፣ የአካልጉዳተኛነቷ ሳያበግራት፣ ህልሟን ለማሳካት እያደረገችው ያለው ጥረት፣ ፍላጎታቸውን እና ምኞታቸውን በማሳካት ጥረታቸው ውስጥ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውንም ነገሮች በመቋቋም ለስኬት መብቃት እንደሚቻል ለወጣት ልጃገረዶች እና ወንዶች ምስክር ሆና የምትታይ ሆናለች። ከተመረቀች በኋላ፣ በመላው አፍሪካ የኢትዮጵያን የባህል አልባሳትን በተለያዩ የፋሽን ዲዛይን የምታስተዋውቅ የአልባሳት ዲዛይን ባለሙያ የመሆን ህልሟ እውን እንዲሆን ትሻለች። በመልካሙ የስኬት ጎዳና ተንደርድራ ህልሟ እውን እንዲሆን እኛም እንመኝላታለን።



ተዋወቁ
ናሆም ፍቃዱ
ፕሮግራም አሶሲየት

ናሆም ፍቃዱ፣ በፋዌ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የስኮላርሽፕ ፕሮግራም ሂደት ውስጥ በማለፍ የተመረቀ የ23 ዓመት ወጣት ነው። ናሆም፣ የተሟጋችነት ባህርይው ከፍተኛ የሆነ፣ ለፈጠራ ሥራ ከፍተኛ ጉጉት ያለው እና ላደገበት ማህበረሰብም የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማድረግ ቀናዒነቱ ያለው ወጣት ነው።በአዲስ አበባ ከተማ ያደገው ናሆም፣ ትምህርቱን ባግባቡ እንዳይከታተል የነበረበትን ከፍተኛ የኑሮ ጫና ተቋቁሞ በማለፍ፣ ከልጅነት እድሜው አንስቶ አካዳሚያዊ እውቀቱን እያዳበረ እና በተለያዩ አጋጣሚዎችም በውስጡ እየጎለበተ የመጣውን የአመራርነት ብቃቱን ለማሳየት የሚታትር ወጣት ነበር። በታዳጊነት እድሜው ስለነበረው የአመራርነት ብቃቱ እንደማሳያ፣የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በተከታተለበት ትምህርት ቤት በተመረጠው ፓርላማ አማካይነት ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ተመርጦ ማገልገሉ ይጠቀሳል። ናሆም፣ ይህን የመሪነት ሚናውን በመጠቀም፣ ትምህርት ቤቱ የመጀመሪያው የሆኑትን የማመሳከሪያ መጻህፍት ባለቤት እንዲሆን የተሳካ ጥረት አድርጓል፤ ለትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በመላ በዋጋ ሊተመን የማይችል የእውቀት ግብዓት የሆነ ቤተመጻሕፍትም እንዲቋቋም የበኩሉን እገዛ አድርጓል።

ናሆም፣ የስምንተኛ ክፍል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ፣ በፋዌ ኢትዮጵያ በኩል ሲተገበር በቆየው የመጀመሪያው ምእራፍ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የስኮላርሺፕ ፕሮግራም እንዲታቀፍ የተደረገበት አጋጣሚ፣ በቀጣይ የትምህርት ጉዞው ወቅት እንደወሳኝ ክስተት ተደርጎ የሚቆጠር ነበር። ይህ የስኮላርሺፕ ፕሮግራም፣ ከገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ የምክር አገልግሎት፣የአመራርነት ስልጠና የሚሰጥ እና በግል የህይወት ጉዞ ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ እድሎች ግንዛቤ የሚፈጥር መሆኑ፣ ለናሆም የወደፊትምኞት ስኬት የነበረው አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። በዚህም መሰረት፣ ናሆም እ.ኤ.አ. 2017 ላይ በጋና በተካሄደው እና በማስተርካርድ ፋውንዴሽን የስኮላርሽፕ ፕሮግራም ውስጥ የቀድሞ እና የወቅቱ ተጠቃሚዎችን እና የፕሮግራሙ አጋሮችን ባሰባሰበው የባኦባብ ጉባኤ ላይ ፋዌ ኢትዮጵያን በመወከል የተሳተፈ ሲሆን፣ አዳዲስ የፕሮጀክት ሀሳቦችን አቅርቧል፤ ከቀድሞው የቦትስዋና ፕሬዝዳንት ከፌስቱስሞጋኢ እና ከሌሎች አንቱ ከተባሉ የጉባኤው ተሳታፊዎች ጋርም ሊገናኝም ችሏል።

ናሆም፣ ባገኘው ከፍተኛ ውጤት መሰረት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርቱን በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የተከታተለ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ዲግሪውንም ከዚሁ ዩኒቨርስቲ በኤሌክትሮ መካኒካል ኢንጂነሪንግ ማግኘት ችሏል። ናሆም፣ በዩኒቨርስቲው ቆይታው ወቅት፣ ተማሪዎችን በ2D አኒሜሽን በማሰልጠን እና ህብረተሰብን መልሶ በማገልገል መርህ መሰረትም በተለያዩ ማህበረሰብ ተኮር ተነሳሽነቶች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አድርጓል። በዚህም መሰረት፣ ናሆም ለፈጠራ እና በተግባር ለተፈተነ የምህንድስና መፍትሄዎች ካለው ፍቅር የተነሳ፣ በፀሐይ ኃይል የሚሠራ አውቶማቲክ የእፅዋት ውሃ ማጠጫ መሣሪያ መፍጠር ችሏል። ይህ ፈጠራው፣ የመመረቂያው ፕሮጀክት ርዕሰ ከመሆኑም በላይ፣ በዩኒቨርሲቲው ኦፊሰላዊ ድረገፅ ላይ በፈጠራ ሥራነት እንደ ምሳሌ ተጠቃሽ ሆኖ ተለጥፏል። ናሆም፣ ከትምህርቱ በሻገር ባዳበረው የተሟጋችነት ባህርይው የተነሳም፣ ከዩኒቨርሲቲው አልፎ የዲጂታል እና የግራፊክ ዲዛይን ችሎታውን በመጠቀም፣ በአረፍት ጊዜው በብሬክ ፍሪ ፕሮጀክት አማካይት በተካሄዱ በወሲብ እና በስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ባተኮሩ ግንዛቤን ማሳደጊያ ማህበራዊን ቅናቄዎች ውስጥም ከፍተኛ ተሳትፎ ነበረው። ናሆም፣ በዚህ ሁለንተናዊ ተሳትፎው የተነሳ፣ ኢትዮጵያን እና የብሬክ ፍሪ ፕሮጀክት ተባባሪ አካላትን በመወከል ናይሮቢ በተካሄደው የአሰልጣኞች ስልጠና (TOT) አውደጥናት ላይ የመሳተፍ እድል አግኝቷል። ዐውደጥናቱ፣ ናሆም በተሟጋችነት ረድፍ ያለውን የአመራርነት አቅሙን የበለጠእንዲያሳይ የረዳው ከመሆኑም በላይ፣ በተሟጋችነትም ሆነ በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ የበለጠ እንዲያጠናክር መደላድል የፈጠረለትም ነበር።

በአሁኑ ጊዜ ናሆም፣ በፋዌ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ውስጥ በሚገኘው የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ተባባሪ ፕሮግራም ውስጥ የፕሮግራሙ ተባባሪ ባለሙያ በመሆን፣ ለፋውንዴሽኑ ፕሮግራም የሁለተኛው ምእራፍ እና ለሌሎች የፋዌ ኢትዮጵያ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ስኬታማ ከንውን በሙያው የበኩሉን እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም፣ የህዝብ ግንኙነት ተግባራትን በማከናወን የድርጅቱን የግንኙነት ጥረቶችን የመደገፍ ተግባራትንም እያከናወነም ነው። እንዲሁም፣ ወጣት ልጃገረዶችን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ በተያዘው ሀገራዊ ራእይ መሰረት፣ ናሆም በትምህርት መዳረስ፣ በቴክኖሎጂ እድገት እና በማህበረሰብ ተፅእኖ ፈጣሪነት መሻሻል ዙሪያ በአበርክቶው በፅናት ቀጥሏል። ባጠቃላይ፣ ናሆም በስኬታማ ጉዞው እና የተለያዩ ተግዳሮቶችን በመቋቋም አብነት፣ ሁልጊዜም ራሱን በትምህርት ለማሻሻል በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ያገኛቸውን ትሩፋቶች ለሌሎች መልሶ ለማጋራት ያለው ፍላጎት በአርአያነት የሚጠቀስ ነው።

ብሬክ ፍሪ ፕሮግራም

የብፌክ ፌሪ ፕሮግራም፣ በኔዘርላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የገንዘብ ድጋፍ በወሲብና በስነተዋልዶ ጤና ዙሪያ በአጋርነት በሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አማካይነት በተመደበ ገንዘብ፣ በፌዌ ኢትዮጵያ አማካይነት አ.ኤ.አ. ጥር 2021 የጀመረ እና 2025 ዓ.ም. ላይም አንዲጠናቀቅ አቅዶ የተያዘለት ነው። ፕሮግራሙ መተግበር ከጀመረበት ጊዜ አንሰቶ የተለያዩ ተግባራት ሲከናወኑ የቆዩ ሲሆን፣ በ2024 ዓ.ም. የ4ኛ ዓመት የትግበራው ሊደት ውስጥም፣ አንዳከፋት ዓመታት ሁሉ ፕሮግራሙን መሰረት ያደረጉ ተግባራት ተተግብረዋል። በመሆኑም፣ በኘካን ኢንተርናሽናል ኔዘርላንድስ፣ በSRHR የአፌሪካ ትረስት (SAT) እና በፌዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት ትብብር እና በሮያል ትሮፒካል ትረስት ኢንስቲትዩት (KIT) እና በሮዛሪያ (Rozaria Memorial Trust / RMT) የቴክኒክ ድጋፌ ጋር በተፈጠረ ጥምረት አየተካሄደ ባለው በዚህ ፕሮግራም፣ በዋናነት በአፌካ አዳሚ ውስጥ በሚገኙ ታዳጊ ሴቶች ላይ የሚከሰትን አርግዝናን እና በሌጅነት የሚካሄዱን ጋብቻን በተመለከተ የአነዚህን በአፌካ አዳሚ ላይ የሚገኙ ወጣትን ግንዛቤ ማሳደግ ላይ ያተኮሩ ተግባራት የህብረተሰቡን ድጋፌ በማማከል ተከናውነዋል።

ኢትዮጵያውስጥ የብፌክ ፌሪ ፕሮግራምን የትግበራ ሊደት፣ ፌዌ ኢትዮጵያ ነኘካን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ እና SAT ን ነማሚወክለው ነወጣት ወንዶች ነርስቲያን ማኅበር ጋር በማስተባበር ላይ ይገኛል።

ቁልፍ ተግባራት እና ስኬቶች



የትምህርት ሚኒስቴር ጥቅምት 2023 ዓ.ም. ላወጣው ረቂቅ አቅጣጫ መሰረት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ፣ በብሬክ ፍሪ ፕሮግራም አማካይነት ከ13 መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የተካሄደውንየጋራ የአድቮከሲ ተግባር መርቷል።ከትምህርት ፖሊሲዎች አንፃር በሴቶች የትምህርት መብት አጠባበቅ ዙሪያ ሊኖሩ የሚችሉ መሰናክሎችን ለመለየት የሚያስችል እና ነባር መረጃዎችን ወይም ሰነዶችን መሰረት ያደረገ የዴስክ ጥናት ተካሂዷል። የዴስክ ጥናቱ ግኝቶች እና አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችም ለትምህርት ሚኒስቴር እንዲቀርቡ ያስቻለ የግንዛቤ ማዳበሪያ ዐውደጥናትም እ.ኤ.አ. ጥር 16 ቀን 2024 ተካሂዷል።

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ከፖላን ኢንተርናሽናል ጋር በመተባበር፣ ከተለያዩ የመንግስት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተውጣጡ 26 ተሳታፊዎችን ያሳተፈ እና በአፍላዎች እና በወጣቶች የወሲብና እና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያተኮረ የምክክር መድረክ እ.ኤ.አ ማርች 22 ቀን 2024 ዓ.ም. አካሂዷል።

40ኛውን "የስርዓተ-ፆታ ጉዳይ የእኔም አጀንዳ ነው" የሚለውን መሪ ቃል መሰረት በማድረግ የካቲት2024 ዓ.ም. በተካሄደው ዓመታዊ ዘመቻ (GIMAC) ላይ በመመሰረት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ በወጣት ሴቶች አመራር ላይ ባተኮረው የሥልጠና ውይይት ላይ ለተሳተፋና በጉዳዩም ዙሪያ የበኩላቸውን የግንዛቤ ሥራ እየሰሩ ላሉ 5 የመብት ተሟጋች ማህበራት፣ ከፖላን ኢንተርናሽናል የአፍሪካ ህብረት የግንኙነት ቢሮ (Plan AULO) ጋር በመተባበር የተለያዩ ድጋፎችን አድርጓል።

ከፖላን ኢንተርናሽናል የአፍሪካ ህብረት የግንኙነት ቢሮ (Plan AULO)፣ከፋዌ አህጉራዊ ጽሕፈትቤት እና በወሲብና በስነተዋልዶ ጤና ዙሪያ ከሚንቀሳቀሰው አፍሪካ ትረስት ጋር በመተባበር፣ በፋዌ ኢትዮጵያ አማካይነት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በወጣቶች የተመራውንና ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህጎች እና አተገባበራቸው አንፃር በየአራት ዓመቱ በተባበሩት መንግስታት አባል ሃገራት የሚካሄደው ሁለንተናዊ ወቅታዊ ግምገማ (UPR) በወጣቶች የተለያዩ መብቶች ላይ በማተኮር እንዲካሄድ ተደርጓል። የግምገማውም ሪፖርትም፣ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን ጽህፈት ቤት ቀርቧል። ከየካቲት 26-28 ቀን 2024 ዓ.ም. ድረስ በተካሄደው በዚህ የግምገማ እና የሪፖርት ዝግጅት ሂደት፣ 30 ወጣቶች ተሳታፊዎች ነበሩ። በተዘጋጀውም ሪፖርት ውስጥም፣ በወሲብና በስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት ላይ በሚስተዋሉው ስምምነቶች እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች እና በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ ወጣቶች በውሳኔ ሰጪነት የሚኖራቸውን ተሳትፎ የሚመለከቱ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርገዋል።

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከዩኔስኮ ጋር በመተባበር፣ በወሲብ እና በስነ ተዋልዶ ጤና በታዳጊ እድሜ በሚከሰት እርግዝና፣ ያለእድሜ በሚካሄድ ጋብቻ እና ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ያተኮረ ዐውደጥናትን ፣ ከግንቦት 15-16 ቀን 2024 ዓ.ም. ድረስ 50 የሃይማኖት እና የማህበረሰብ መሪዎችን በማሳተፍ እንዲካሄድ አድርጓል። እ.ኤ.አ. ግንቦት 27 ቀን 2024 ዓ.ም. ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ያለእድሜ በሚካሄድ ጋብቻ፣ በታዳጊ እድሜ በሚከሰት እርግዝና)፣ እና ጥራት ያለው ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ ላይ እና በወሲብ እና በስነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ መረጃ ከማግኘት አንፃር የሚስተዋሉ ችግሮችን እና ተግዳሮቶችን መሰረት ያደረገ የወጣቶች ፖሊሲ እንዲዘጋጅ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል።

እ.ኤ.አ. ነሀሴ 2024 ዓ.ም. በተካሄደውና ያለእድሜ ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም በማለም ለተመሰረተው ብሄራዊ የትብብር ህብረት እውቅና መስጠት ላይ በማተኮር የተካሄደውን ዐውደጥናት መሰረት በማድረግ፣ በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ የተለያዩ አደጋዎች መንስዔነት በአማራ ክልል የተስተዋለው የአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ለረጅም ጊዜ ተዘግቶ የመቆየት ሁኔታ፣ የተወሰኑ የክልሉን ልጃገረዶች ካለእድሜ ጋብቻ እና ለመሰል አሉታዊ ችግሮች ሊያጋልጣቸው ስለሚችልበት ሁኔታ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ተገቢውን የማንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሠርቷል።

በተመሳሳይም፣ በአማራ ክልል የተከሰቱ የተለያዩ ሰውሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች በሴት ተማሪዎች ላይ የሚያስከትሏቸውን የተለያዩ ችግሮችን፣ በዚህ ችግር የተነሳም በክልሉ የምዕራብ ጎጃም ዞን እየታየ የመጣው ያለ እድሜ ጋብቻ በምሳሌነት የቀረበበት ዐውደ ጥናት፣ ጥቅምት15 ቀን 2024ዓ.ም. በክልሉ ተካሂዷል።

ፋዌኢትዮጵያ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበረውን የሴት ልጅ ቀንን ጥቅምት 17 ቀን 2024 ዓ.ም. ያከበረ ሲሆን፣ በአለቱም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ 59 አካላትን ያሳተፈ የፓናል ውይይት በሴቶች ትምህርት፣ በተለይም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ወጣቶች በማብቃት ላይ በማተኮር ተካሂዷል።



ተዋወቁ

ማሪያ አንዷለም

የብሬክ ፍሪ የወጣት መብት ተሟጋች

በከፍተኛ የእድገት እንቅስቃሴ ውስጥ ባለችው የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ውስጥ የምትኖረው የ21 ዓመቷ ማሪያ አንዱዓለም፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ታዳጊዎች ካልተፈለገ እርግዝና እና ያለእድሜ ጋብቻ ራሳቸውን እንዲከላከሉ የበኩሏን አስተዋፅኦ እያደረገች ትገኛለች። ለእነዚህ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ እነዚህን የማህበረሰቡ አካላትን ፍላጎት እና መብት በዕናት በመደገፍ፣ ማሪያ ለለውጥ በከፍተኛ ደረጃ ድምፃቸውን ከሚያሰሙ ወገኖች አንዷ ሆና ብቅ ብላለች። ማሪያ ለእነዚህ ተጋላጭ ወገኖች የተሟጋችነት ጉዞዋን የጀመረችው፣ በብሬክ ፍሪ ፕሮጀክት አማካይነት በተቋቋመው የወጣቶች የመብት ተሟጋች ቡድን ውስጥ ተቀላቅላ መሳተፍ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ነው። ይህን ተሳትፎዋን መሰረት በማድረግም፣ በአፍላ እድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ላልተፈለገ እርግዝና እና ያለእድሜ ጋብቻ እንዲዳረጉ የሚያደርጓቸውን ችግሮች፣ እንዲሁም እነዚሁ ችግሮች በወጣቶቹ ላይ በቀጣይ የህይወት ጉዟቸው ውስጥ ስለሚያሳድሩባቸው ተፅእኖዎች በጥልቀት ተረድታለች።

ማሪያ ይህ የተሟጋችነት ጉዞዋ ለፍትህ ጠንካራ አቋም እንዲኖራት የሚያደርጋትን ስሜት እንድታዳብር ያደረጋት ከመሆኑም በላይ፣ በዚሁ የፋዌ ኢትዮጵያ የብሬክ ፍሪ ፕሮጀክት ዓላማ መሰረት በታዳጊ እድሜ ላይ ያሉ ልጆች፣ ባልተፈለገ እርግዝና እና ካለእድሜ ጋብቻ የተነሳ የሚደርሱባቸውን ችግሮች አስቀድመው እንዲያስተውሉ እና የችግሮቹም ሰለባ እንዳይሆኑ የሚያስችላቸውን ግንዘቤ በመፍጠር ሂደት ውስጥ ለለውጥ በቁርጠኝነት መሳተፍ እንዳለበት አስገንዝቧታል። በዚህም መሰረት፣ በብሬክ ፍሪ የተነሳሽነት ግብ መሰረት ውሳኔ ሰጪ የሆኑ አካላት እና በቀጥታ ከእነዚህ ታዳጊዎች ችግሮች ጋር በተያያዘ ተሳትፎ ያላቸው ወገኖች፣ እነዚህን ታዳጊዎች ከሚያጋጥሟቸው እነዚህን መሰል ችግሮች የሚታደጉ፣ ህይወታቸውንም በቀና መንገድ መምራት እንዲችሉ የሚያግዟቸው ተግባራትን ሥራ ላይ እንዲያውሉ ማሪያ ቁርጠኛ አቋም ያላት መሆኑንአሳይታለች።

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አዘጋጅነት በተካሄደው 5ኛው ሀገር አቀፍ የአፍላ ወጣቶች እና የወጣቶች ጤና መድረክ (NAYHF) ላይ በመሳተፍ፣ ማሪያ የመድረኩ ተሳታፊ በመሆን ተሞክሮዋን መሰረት ያደረገ አስተዋፅኦ በማድረግ ተሳትፋለች። "ተደራሽነትና ዋራት፡ ለሁሉም በአፍላ የእድሜ ክልል ላሉ ታዳጊዎች እና ወጣቶች ምላሽ ሰጪ የጤና ሥርዓት" በሚል መሪ ቃል በተካሄደው በዚህ መድረክ ላይ፣ የመንግሥት ተወካዮች፣ ዓለም አቀፍ አጋር ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተለያዩ ኤጀንሲዎች፣ የህክምና ባለሙያዎች እና ምሁራን የተሳተፉ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊዎችን እና ወጣቶችን ጤና እና ደህንነት ነክ ችግሮችን በጋራ መፍታት ላይ ትኩረቱን ያደረገ መድረክ ነበር።

ማሪያ፣ ያለእድሜ ጋብቻ እና በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ያለ እርግዝና ለሚያስከትሏቸው ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ታዳጊ ወጣቶችን ድምፅ አጉልታ ለማቅረብ መድረኩ እድል የሰጣት ከመሆኑ በተጨማሪ፤ በመድረኩ ሂደት ወቅትም መድረኩን የመምራት እድልም ያገኘችበትም ነበር። በዚህ መድረክ የመምራት አጋጣሚዋም፣ የወጣቶች የተለያዩ ፍላጎቶች እና አመለካከቶች በመድረኩ በሚገባ እንዲንፀባረቁም ሚናዋን ተጫውታለች። በዚህ መድረክ ሂደት ውስጥ፣ ማሪያ፣ ታዳጊዎች እና ወጣቶች በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ከሚከሰት እርግዝናም ሆነ ካለእድሜ ጋብቻ ተግዳሮቶች ነፃ መውጣት እንዳለባቸው በማሳሰብ የተሟጋችነት አቅሟን አሟጣ ተጠቅማለች።

ባጠቃላይ ማሪያ፣ መንግስት የታዳጊዎችን እና ወጣቶችን ፍላጎት የሚያሟሉ ውጤታማ ህጎችን እንዲያወጣ የተለያዩ አጋጣሚዎችን መጠቀሟን አጠናክራ እንደምትቀጥል ትናገራለች። እንዲሁም፣ ማሪያ በማግባባት እና በተሟጋችነት ያዳበረችውን ልምድ ያለእድሜ ጋብቻንም ሆነ የጉርምስና ወቅትን ያልተፈለገ እርግዝናን በተመለከተ በቀጣይነት ያለማቋረጥ የምታደርገውን ጥረት ከእስካሁኑ በበለጠ ድምፅ በማጉላት ትቀጥላለች። በተለይም፣ ለአደጋ የተጋለጡ ወጣት ልጃገረዶችን በተለያዩ መልኩ የመደገፍ ዕናቷን እና በጎ ተፅእኖዋን ለማስፋት በፅኑ ትሻለች።

ሜክ ዌይ ፕሮጀክት

የሜክ ዌይ ፕሮጀክት፣ አ.ኤ.አ. ከ2021-2025 ዓ.ም. ድረስ እንዲከናወን የታቀደ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ፕሮጀክቱ በ4ተኛው የፕሮጀክቱ የትግበራ ዓመት ካይ የሚገኝ እና በኔዘርላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የገንዘብ ድጋፍ አማካይነት በወሲብ እና በስነተዋልዶ ጤና ዙሪያ በሚንቀሳቀስ የሲጋርነት ፈንድ በዘላቂ ልማት ግብ 5 አማካይነት አተተገበረ ያከ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ በዋናነት ትኩረት ሰጥቶ አየተተገበረ ያከው፣ በወሲብና እና በስነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ያኩ የተከያዩ ችግሮች መፍትሄ ኪያገኙ የሚችኩት ሁኩን አቀፍ ችግሮችን የመከየትና መፍትሄ የመስጠት ስልትን በማስተዋወቅ ካይ ትኩረት በመስጠት ሲሆን፣ በ5 የአፈሪካ ሀገራት አየተተገበረ ይገኛል። በኢትዮጵያ የዚህ ፕሮጀክት ትግበራ፣ በቪኤስኦ የኢትዮጵያ ጽሕፈት ቤት በቪኤስኦ አስተባባሪነት እና በፌዌ ኢትዮጵያ፣ በኢፓስ (Ipas) እና ነከባርኤችኤ (CORHA) አጋርነት በተፈጠረ ጥምረት በኦሮሚያ፣ በደብረ ብርሃን፣ በተፈናቃይ ማዕከከት እና በአዲስ አበባ በመተግበር ካይ ይገኛል።



ቁልፍ ተግባራት እና ስኬቶች

በጤና፣ በማህበራዊ እና በህግ ጉዳይ ላይ ከሚሠሩ ማህበራት፣ ከመገናኛ ብዙሃን እና ከወጣት አደረጃጀቶች የተውጣጡ 44 ተሳታፊዎች (29 ወንድ፣15 ሴት) የተሳተፉበት እና ከወሲብ እና ከስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የመገለል አደጋ የተጋለጠባቸውን ወጣቶችን በተመለከተ ማግባባት ላይ እና ግንዛቤ ማሳደግ ላይ ያተኮረ ዐውደ ጥናት ተካሂዷል።

በተቋማዊ የአቅምምዘና ላይ በመመሰረት፣ በክትትል እና ግምገማ እና በኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂላይ ያተኮረ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ለቆዌ ኢትዮጵያ ተባባሪ አካላት ለሆኑት፣ ለወጣት ወንዶች ክርስቲያን ማህበር (YMCA) እና ለ EYF ተሰጥቷል። ይህ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና የስልጠናውን ተሳታፊ ድርጅቶችን አቅም በማጠናከር አስተዋፅኦ ያደረገ ሲሆን፣ ለሁለቱም ድርጅቶች የሚያገለግል የኮሙዩኒኬሽን የስትራቴጅ ማኑዋሎችን ለማዘጋጀት ረድቷል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተተገበሩ ያሉ ፖሊሲዎችን ማስተዋወቅ ላይ ያተኮረ ስብሰባ፣ በእነዚህ ፖሊሲዎች የትግበራ ሂደት በግንባር ቀደምትነት ከሚሳተፉእና የፖሊሲ ሃሳቦችን ከሚያመነጩ አካላት ጋር ተካሂዷል። በስብሰባው፣ ከወሲብ እና ከስነ ተዋልዶ ጤና አንፃር በጤናጣቢያዎች ከሚሰጡ አገልግሎቶች አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ችግሮች የተነሳ መገለልም ለሚደርስባቸው ወጣቶች፣ በጤና ተቋማት ሥራ ላይ ሊውል የሚችል የኢንተርሴክሽናል ማህበረሰብ አቀፍ የውጤት መስጫ ካርድ እንዲጠናቀቅ ተደርጓል።

ከሀገር አቀፍና ከክልል የወጣት አምባሳደሮች፣ ከወጣት ምክርቤቶች እና በተለያዩ ምክንያች የመገለል ተፅእኖ ሥር ካሉ ወጣቶች ጋር በተሚጋችነት ተግባር ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ ተካሂዷል። በዚሁ የውይይት መድረክ ላይ የተለያዩ ጥናቶች ግኝቶች እንዲተዋወቁ ተደርገዋል፤ ከማግባባትና ከተሚጋችነት ተግባራት አንፃር ሊደረጉ የሚገባቸውን ጥረቶች የተመለከተ የትግበራ እቅድ ንድፍም እንዲቀርብ ተደርጓል።

ከዚህ የውይይት መድረክ በተጨማሪም፣ አብዛኞቹ ከወሲብ እና ከስነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ በተለያዩ ድርጅቶች የአጋርነት ፈንድ የተያዙ ፕሮግራሞች እ.ኤ.አ. በ2025 ዓ.ም. ላይ የሚጠናቀቁ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ፣ በእሳካሁኑ የፕሮግራሞቹ የአተገባበር ሂደት ውስጥ ስለተመዘገቡ ውጤቶች እና ፕሮግራሞቹም በዘላቂነት በፋይናንስ ስለሚደገፉባቸው ሁኔታዎች እና በቀጣይነትም ሊገኙ በሚችሉ የገንዘብ የድጋፍ አማራጭ አቅሞች ዙሪያ ያተኮረ የልምድ ልውውጥ ስብሰባም ተካሂዷል።

በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን መከላከል እና ማስቆም ላይ በማተኮር በየዓመቱ የሚካሄደውን የ16 ቀናት ዘመቻ መሰረት በማድረግ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ፣ በሜክ ዌይ እና በብሬክ ፍሪ ፕሮጀክቶቹ አማካይነት ሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን (GBV) እና በትምህርት ቤቶች ውስጥም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሊከናወኑ የሚገባቸውን የመከላከል ተግባራትን የተመለከተ ሥነሥርዓት ታህሣሥ 2024 ዓ.ም. አካሂዷል። 55 ተሳታፊዎችን በማሳተፍ በተካሄደው በዚህ ሥነሥርዓት ላይም ከዘመቻው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት ተካሂዷል። የፓናል ውይይቱ ይዘትም ተደራሽ እንዲሆን ለማስቻል፣ ፋና በተሰኘው ሀገር አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት የሥነሥርዓት ሂደቱ እንዲተላለፍ ተደርጓል።



የሜክዌይ ፕሮጀክትተፅዕኖ አንዱ ማሳያ

ከተጋላጭነትወደ ተሟጋችነት የተደረገ ሽግግር

ሄኖክ፣ ቶሌራ፣ ዮናታን፣ አንተነህ እና ቤተልሄም፣ በአዳማ ከተማ ውስጥ የሚገኙ እና ወጣቶችን በማህበራዊ ኃላፊነት ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በተቀረፀው የሜክ ዌይ ፕሮጀክት ውስጥ በበጎፈቃድ ተዋናይነት በጋለ ስሜት እየተሳተፉ ያሉ ወጣቶች ናቸው። እነዚህ የበጎ ፈቃድ ተዋናይ ወጣቶች፣ በዚህ የበጎ ፈቃድ ተግባራቸው ውስጥ በንቃት እና በቁርጠኝነት ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች፣ በወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር አማካይነት ተሰጥቷቸዋል። እነዚህ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በስልጠና ባገኙት ግንዛቤ አማካይነት፣ በማህበረሰብ ተኮር የበጎ ፈቃድ ተሳትፏቸው የተለያዩ ተግባራትን በንቃት አከናውነዋል። ከዚህ አኳያ በተለይ፣ የወሲብ እና የስነተዋልዶ ጤና የተመለከቱ የተለያዩ ስልጠናዎችን በአፍላ እድሜ ውስጥ ላሉ ወጣቶች ከመስጠታቸውም በላይ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን አስፈላጊ ከሆኑ የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ጋር በማገናኘት በማህበረሰባቸው ውስጥ ከፍተኛ እመርታዊ ለውጥ እንዲመጣ የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

በፋዌ ኢትዮጵያ በኩል እየተተገበረ ያለው የሜክ ዌይ ፕሮጀክት፣ የወጣቶች ፍላጎትን ከጤና ሥርዓት አስተዳደሩ ጋር በማቀናጀት፣ ለወጣቶች በተለይም የመገለል እጣ ለሚደርስባቸው ወጣቶች ሁሉን አቀፍና ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት ተደራሽ በሚሆንበት ሁኔታ ላይ በማተኮር የሚተገበር ፕሮጀክት ነው። በዚህ ፕሮጀክት ዓላማ መሰረትም፣ ሄኖክ፣ ቶሌራ፣ ዮናታን፣ አንተነህ እና ቤተልሄም፣ እ.ኤ.አ. በ2024 ዓ.ም. በኢንተርሴክሽናል የማህበረሰብ ውጤት ካርድ (Intersectional Community Scorecard/ ICSC) አተገባበር ላይ ያተኮረ ስልጠና ለአምስት ቀናት ከወሰዱበኋላ፣ ለተለያዩ ሁኔታዎች ተጋላጭ ከሆኑ ወጣቶች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ውስጥ ወሳኝነት ባለው ተግባር ውስጥ መሳተፍ በሚያስችላቸው ማህበረሰብ ተኮር የተጠያቂነት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ውስጥ እንዲቀላቀሉ ሆነዋል። የሜክ ዌይ ፕሮጀክት አንዱ አካል በሆነው እና ተሳትፎ በሚያደርጉበት በዚህ የማህበራዊ ተጠያቂነት ተግባራቸው፣ ከትምህርት እጦት፣ ከዘር መድልዎ፣ ከአእምሮ ጤና ችግር፣ ከድህነት እና በተለያዩ ጥቃቶች ከሚደርሱ ችግሮች ጋር በተያያዘ ለተደራራቢ ችግሮች ወይም አስጊ ለሆኑ ሁኔታዎች ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶች፣ የኢንተርሴክሽናል ማህበረሰብ የውጤት ካርድ ሂደት ውስጥ በመሳተፍ በወሲብና በስነተዋልዶ ጤና ጥብቅና እንዲቆሙ የበኩላቸውን እገዛ አድርገዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ።

እነዚህ በጎፈቃደኛ ወጣቶች፣ ለወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል በአገልግሎት ተጠቃሚዎች እና በአገልግሎት አቅራቢዎች መካከል ያለውን መስተጋብር በማበረታታት ረገድ ተጨባጭ ውጤቶችን ለማቅረብ ከተዘጋጁት የማህበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎች አንዱ በሆነው በኢንተርሴክሽናል ማህበረሰብ የውጤት ካርድ ሂደት ውስጥ በተሰጣቸው ስልጠና መሰረት ራሳቸውን ዝግጁ አድርገው ተንቀሳቅሰዋል። በዚህ እንቅስቃሴያቸውም፣ ማህበረሰቡን በማንቃት እና በማስተባበር፣ በበርካታ የተወሳሰቡ ተጋላጭነቶች ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች ትክክለኛውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በማመቻቸት እና በተሰጡ አገልግሎቶች ዙሪያም እነዚሁ ወጣቶች እና አገልግሎት ሰጪዎቻቸው የትኩረተ ቡድን ውይይት (FGDs)፣ እንዲሁም የራስ ግምገማ እንዲያካሂዱ የሚያስችሉ ተግባራትን አከናውነዋል።

በነዚህ ጥረቶቻቸው የተነሳም፣ እነሄኖክ ለወጣቶች ድምፅ እና ጠበቃ ሆነው ብቅ ከማለታቸውም በተጨማሪ፣ደህንነታቸው የተጠበቀ የአገልግሎት መስጫ ሥፍራዎች እንዲዘጋጁ እና ለወጣቶች ተስማሚ የሆኑ የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ተደራሽ ስለሚሆኑበት ሁኔታ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎችን ሠርተዋል።

በዚህ ስኬታማ ተግባራቸው የተነሳም፣ ይህ ስኬታማ ተግባራቸው አዳማ ከተማ በሚገኘው ቢፍቱ ጤናጣቢያ ምማስፋት እንዲቻል፣ ተሞክሯቸውን መሰረት ያደረገ ገለፃ ለአካባቢው ባለስልጣናት እና ውሳኔ ሰጪ አካላት አቅርበዋል። ይህት ርጉም ያለው ተሳትፏቸው፣ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ዘንድ አድናቆትን ያተረፈ በመሆኑ፣ በሀገርአቀፍ ደረጃ ከአድቮከሲ ጋር በተያያዘ በተካሄዱ የተለያዩ ስብሰባዎች ላይም በመልካም ተሞክሮነት እንዲጋራ ሆኗል።እንዲሁም፣ በተግባር የተፈተሸውን ይህን የእነሄኖክን ስኬት መሰረት በማድረግም፣ በአዳማ ከተማ ያሉ ባለስልጣናት ከወጣቶች የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ይህን የኢንተርሴክሽናል ማህበረሰብ የውጤት ካርድ አተገባባርን እንደ አንድ ስልት መጠቀም ጀምረዋል።

FAWE Forum for African Women Educationalists
Forum des éducatrices africaines

ቱሰሜ ፕሮጀክት

በፉዌ አሀጉራዊ ጽ/ቤት የተጀመረው የቱሴሜ ፕሮጀክት፣ በኡጋንዳ፣ በኬንያ እና በኢትዮጵያ ውስጥ በስደተኞችና በሀገር ውስጥ በሚኖሱ ሰው ሠራሽ ችግሮች የተነሳ በሚፈናቀሉ (IDP) ማህበረሰቦች ውስጥ የፆታ አንኳልነትን እና ማህበራዊ ተሳትፎን መሰረት በማድረግ እ.ኤ.አ ከሚያዚያ 2024 ዓ.ም እስከ መጋቢት 2027 ዓ/ም ድረስ እየተተገበረ ያለ ፕሮጀክት ነው። ከIDRC-KIX፣ ከፉዌ አሀጉራዊ ጽ/ቤት፣ ከHERS-EA እና ከASER ጋር በመተባበር በሚተገበረው በዚህ ፕሮጀክት፣ የቱሰሜ ፕሮግራምን ስደተኛ እና ተፈናቃይ የሆኑ ልጆችን በሚያስተናገዱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መጠቀም አንዲቻል፣ ከሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የትምህርት አሰጣጥ (GRP) እና ከልህቀት ማዕከላት (COE) ጋር በተዛመደ የቱሴሜ ትግበራ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነበረውን ፈይዳ የተመለከተ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር (Action research) ይካሄዳል። ፕሮጀክቱ ከዚህ በተጨማሪም፣ ከስደተኛ እና ተፈናቃይ ከሆኑ ወገኖች የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶችን ባማከለ ሁኔታ የተሻሻሉ የቱሴሜ መተግበሪያ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት፣ በአነዚህ ማዕከላት ውስጥ ያሉ ልጆች በትምህርት፣ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ አድገታቸውና ተሳትፏቸው ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ መሰናክሎችን መከየት የሚያስችላቸውን ክህሎት አንዲያገኙና የሚያጋጥሟቸውንም ችግሮች መፍታት የሚያስችላቸውን አቅም በማጎልበት ላይም ያተኩራል። ፕሮጀክቱ፣ የመጠከል ሁኔታ ውስጥ ባሉ በአነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ አንኳልነትን እና ማህበራዊ ተሳትፎን ከማሳደግ አኳያ፣ አዳዲስ የተግበራ ስልቶችን በየጊዜው በመቀየስ የመተግበር ዓላማም አለው።

ቁልፍ ተግባራት እና ስኬቶች

ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ የቱሰሜን ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ፣ ከስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት (RRS) እና ከደብረብርሃን ከተማ የገንዘብና የትምህርትጽ/ቤቶች ጋር ስምምነት ተፈራርሟል። ይህ የአጋርነት ስምምነት፣ በሀገር ውስጥ ተፈናቃይ ማህበረሰቦች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታእኩልነትን እና ማህበራዊ ተሳትፎን ማሳደግ ላይ ያለመነው።

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ በፕሮጀክቱ የትግበራ እቅድ መሰረት፣ ከሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የትምህርት አሰጣጥ (GRP) እና ከልህቀት ማዕከላት (COE) ጋር በተዛመደ፣ የቱሴሜ ትግበራ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነበረውን ፋይዳ የተመለከተ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር (Action research) ለማካሄድ የሚያስችለውን የሙያ ፈቃድ ከኢፌዲሪ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አግኝቷል። ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስችሉ መጠይቆች ተዘጋጅተውም፣ ብቃታቸውን የተመለከተ ፍተሻ በፋዌ ኢትዮጵያ አስተባባሪነት በHERS-EA መሪ ተመራማሪ አማካይነት ተደርጎባቸዋል።



የኢግናይት ፕሮጀክት

የኢግናይት ፕሮጀክት፣ ፊዌ ኢትዮጵያ የተለያዩ ተግባራቱን በገንዘብ ከመደገፌ አያደረገ ባለው ዋረት ውስጥ በስኬት የዳርጅቱ አካል የሆነ ፕሮጀክት ነው። አ.ኤ.አ. ነዱካይ 2024 አስከ ታህሣሥ 2025 ዓ.ም. የሚቆየው እና በዩኤኤፎ አፍሪካ (UAF Africa) የገንዘብ ድጋፌ የሚደረግለት ይህ ፕሮጀክት፣ ሥርዓተ-ፆታን ታሳቢ ያደረጉ አካባቢዎችን በመፌጠር እና በትምህርት ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ማህበራዊና ባህላዊ አንቅፉቶችን በመፍታት፣ ከተለያዩ ችግሮች ተጋለጭ የሆኑ በአፍላ አዳሜ ውስጥ የሚገኙ ልጃገረደች በትምህርት እና በጤና ረገዱ የሚያጋጥሚቸውን ችግሮች በማሻሻል ላይ ትኩረት አድርጎ የሚተገበር ነው። በአማራ ብ/ክ/መ በሰሜን ጎጃም ዞን በአምስት ቀበሌዎች አየተተገበረ ያለው ይህፕሮጀክት፣ በሶስት ዋና ዋና አካሣዎች ላይ ያተኮረ ነው።

- ልጃገረደች በተለያዩ የትምህርት አደሎች ውስጥ አንዲሰተፋ በማድረግ ረገዱ ወላጆች የበኩላቸውን ዋረት አንዲያደርጉ በማህበረ-ባህላዊ እና በኬሎች አደናቃፊ ሁኔታዎች የተነሳ የሚደርሱባቸው አሉታዊ ጫናዎች አንዲቀረፋ ዋረት ማድረግ፣
- በማናቸውም ሁኔታዎች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ተገቢው ስፌራ አንዲሰጣቸው፣ የትምህርት እና ኬሎች ሁኔታዎች ከሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጡ አንዲሆኑ፣ በአጠቃላይም ሥርዓተ-ፆታን የሚመለከቱ ጉዳዮች የተሻሻለ ገፅታ አንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በአፍላ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረደች፣ የተሻለ የፆታ እና የሥነተዋልዶጤና (SRH) ትምህርት እና አገልግሎት አንዲያገኙ ማድረግ የሚሉት ናቸው።

ቁልፍ ተግባራት እና ስኬቶች

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ፕሮጀክቱን በተያዘለት እቅድ መሰረት በፕሮጀክቱ የትግበራ አካባቢ በውጤታማነት ማጠናቀቅ የሚያስችለውን የመግባቢያ ሰነድ፣ ከሰሜን ጎጃም ዞን ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ እና ከፋይናንስ እና ከትምህርትጽ/ቤቶች ጋር ተፈራርሟል።

እ.ኤ.አ. ከህዳር 16 እስከ 18 ቀን 2025 ዓ.ም. ድረስ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ በሰሜን ጎጃም ዞን፣ ከባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ አምስት ቀበሌዎች ለተውጣጡ 15 ተሳታፊዎች (6ቱ ሴቶች ናቸው) በልጆች ጥበቃና መከላከል ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጥቷል። ስልጠናው፣ በልጆች ጥበቃና መከላከል ላይ ከሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ኮሚቴዎች አባላት እና ከመምህራን ጋር የተካሄደ ሲሆን፣ በመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ የሚያጋጥሙ መሰናክሎችን በመቅረፍ ላይ ከማተኮሩም በላይ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱ ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ትኩረት የሚሰጥ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ተግባራት እና በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የተለያዩ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በመቅረፍ ሂደት ውስጥ የማህበረሰብ አቀፍ የልጆች ጥበቃ ኮሚቴዎች የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ ማጠናከር ላይ ያተኮረ ነበር።

የትማር እንግዳ፡- እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)

እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነልቦና ተባባሪ ፕሮፌሰር ሲሆኑ፣ በዩኒቨርስቲው የስርዓተ-ፆታ ጥናት ማዕከል እና የስነ ልቦና ትምህርት ክፍል የማስተማር እና የምርምር ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ። ከ20 ዓመታት በላይ በማስተማር እና በምርምር ልምድ ያላቸው ዶ/ር እመቤት፣ በኢትዮጵያ አንጋፋ የሆነውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን የመጀመሪያዋ ሴት የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዳንት በመሆን በማገልገላቸው ይታወቃሉ። ዶ/ርእመቤት ከዚህ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አገልግሎታቸው በተጨማሪ፣ ከቤተሰብ፣ ከልጆች እናከስርዓተ-ፆታ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን በምርምር፣ በምክር፣ በስልጠና እና በማማከር የማቅረብ ዓላማን በማንገብ እየተንቀሳቀሰ ያለው የ "ኒያ የህፃናት እና የቤተሰብ ልማት ማዕከል (Nia Center for Children and Family Development NiaCCFD)" መስራች እና ዳይሬክተር ናቸው። ዶ/ር እመቤት ሙሉጌታ፣ በተለያየ መልኩ ምሁራዊ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ሲሆኑ፣ በተለይም በድህነት እና በልጆች የጉልበት ብዝበዛ፣ በፆታ እና ትምህርት የተለያዩ ጉዳዮች፣ በፆታ እና ድህነት ግንኙነት እና ከልጆች ጋር በተያያዙ የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ መጣጥፎችን እና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በተለያዩ መድረኮች አቅርበዋል፤ አሳትመዋል።



በዚህ የትማር መዕሄት እትማችን፣ ዶ/ርእመቤት ሙሉጌታን በእንግዳ አምዳችን ላይ አቅረበናቸዋል። በመሆኑም፣ የግል ጉዟቸውን፣ ልምዳቸውን፣ ስኬታቸውን እና በአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች መድረክ (FAWE Ethiopia Chapter)እና በፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር (FAWE Ethiopia Chapter) ስኬቶች ስላበረከቱት ጉልህ አስተዋፅኦ በቀጣዩ ቃለመጠይቅ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ትማር፡- ለመጽሐፍትን አንባቢዎች ራስዎን ቢያስተዋውቁልን? (አጠቃላይ የህይወት ታሪክዎን፣ የትምህርት ሂደትዎን፣ የስራልምድዎን እና በፋዌ ኢትዮጵያእና በፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት ውስጥ ስላደረጉትና እያደረጉት ስላለው ተሳትፎ በማካተት)

እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፡- እመቤት ሙሉጌታ እባላለሁ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሥነልቦና ትምህርት ቤት ተባባሪ ፕሮፌሰር ነኝ። በዩኒቨርሲቲው የሥርዓተ-ፆታ ጥናት ማዕከል ኮርሶችን አስተምራለሁ። በተለያዩ የማህበረሰብ አቀፍ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት እሳተፋለሁ፤ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያም ጥናትና ምርምሮችን አደርጋለሁ።

የትምህርት ሁኔታዬን በተመለከተ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ቅድስት ማርያም ንግድ ሥራ ኮሌጅ ተከታትያለሁ። በሁለተኛ ደረጃ ማጠቃለያ ፈተና ባገኘሁት ውጤቴም መሰረትም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብቼ በስነልቦና የትምህርት መስክ በቢኤ ዲግሪ ተመርቄያለሁ። የኤምኤ ዲግሪዬን ደግሞ፣ አሜሪካ ኦሃዮ ከሚገኘው ከሲንሲናቲ ዩኒቨርስቲ በ"ማስተር ኦፍ ኢጁኬሽን" ያገኘሁ ሲሆን፣ የፒኤችዲ ዲግሪዬን ደግሞ ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ በ"ዶክተር ኦፍ ኢጁኬሽን" አግኝቻለሁ።

የሥራ ልምዴን በተመለከተ፣ በሥራው ዓለም ከ30 ዓመታት በላይ ያሳለፍኩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነው። የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንትነትን ጨምሮየ ተለያዩ ኃላፊነቶችን በመያዝ ዩኒቨርስቲውን አገልግያለሁ። በተራ አባልነት እና በቦርድ አባልነት በበርካታ ድርጅቶች ውስጥ በንቃት ተሳትፌያለሁ። ለዚህም ፍላጎቴን መሰረት ባደረገ ሁኔታ፣በማህበራዊ ጥናት መድረኮች፣ በኢትዮጵያ ሳይኮሎጂስቶች ማህበር፣ በፋዌ ኢትዮጵያ እና በፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት ያደረኩት እና እያደረኩት ያለው ተሳትፎ ተጠቃሽ ነው። በተጨማሪም፣ በተለያዩ ሀገራት ውስጥ በምርምር ባልደረባነት የመሳተፍ እድል አግኝቻለሁ፤ ከርዌይ እና ስዊድን ባሉአጋሮች በተተገበሩ ፕሮጀክቶች ውስጥም እንዲሁ በተባባሪነት ተሳትፌአለሁ።

በመሃል በተለያየ ምክንያት ከማቋረጤ በፊት፣ ለአንድ የአገልግሎት ዘመን በፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት ውስጥ በቦርድ አባልነት ተሳትፌአለሁ። አሁን በቅርቡ፣ በሁለተኛው የአገልግሎት ዘመኔ፣ በድጋሚ የአህጉራዊውን ጽቤት በቦርድ አባልነት እና የክብር ፀሀፊ በሚል ማእረግ እያገለገልኩ እገኛለሁ። በቀድሞ የስልጣን ዘመኔ፣ የዚህ የፖንአፍሪካ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት የቦርድ አባል ከመሆኔ በተጨማሪ፣ በክብር ትሬጀርነትም አገልግያለሁ።

ከፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ጋር የተዋወኩት በግል ከመስራቾቹ ጋር በነበረኝ ግንኙነት ነው። ከዚህ ትውውቁ በኋላ፣ አባል ሆንኩኝ፤ በመቀጠልም ቻፕተሩን በሰብሳቢነት መምራት ችያለሁ። ባጠቃላይም፣ ለስድስት ዓመታት ቻፕተሩ ውስጥ በቦርድ አባልነት እና በቦርድ ሰብሳቢነት ተሳትፌአለሁ። በተጨማሪም፣ የጥናትና ምርምር አቅምን የሚገነባ ተነሳሽነትን በመውሰድ እና በርካታ ከሚቴዎችን በመምራት ለፋዌ ኢትዮጵያ የበኩሌን አስተዋፅኦ አድርጌአለሁ። በዚህ ቆይታዬ ወቅት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ያጋጠሙትን የተለያዩ ተግዳሮቶችን እና ችግሮችን ያለፋታ በመቋቋም ያልተቋረጠ ለውጥና እድገት ማስመዝገብ መቻሉን ማስተዋል ችያለሁ።

በፋዌ እና በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ በነበረኝ እና ባለኝ ተሳትፎ እናበራሴም የግል ጥረት የሴቶችን ትምህርት በሚመለከቱ የተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ በቁርጠኝነት ተንቀሳቅሻለሁ። የዚህ ቁርጠኝነቴ መሰረቱ፣ ልጃገረዶች በአጠቃላይም ሴቶች የሚጋጥሟቸውን የተለያዩ ተግዳሮቶችን በአሸናፊነት መወጣት እና ያላቸውንም ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም እንዲችሉ፣ እንዲሁም እራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን በብቃት መደገፍ የሚችሉበት አቅም እንዲኖራቸው ከትምህርት እና ከማብቃት ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ ተግባራት አይነተኛ አስተዋፅኦ አላቸው የሚል የፀና እምነት አለኝ።

ትማር፡- የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር መስራች አባል በመሆንዎ፣ እስካሁን በቻፕተሩ ያስተዋሏቸውን ጉልህ ለውጦች እና እድገቶች በዝርዝር ቢያብራሩልን?

እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፡- ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ፣ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ በእድገት ሂደቱ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል። እንደሚታወቀው፣ ቻፕተሩ እውን የሆነው ክብርት አምባሳደር ዶ/ር ገነት ዘውዴ የትምህርት ሚኒስትር፣ ክብርት ወ/ሮ የልፍኝ ወርቁ ደግሞ በተመሳሳይ ጊዜ የሚኒስቴሩ የሴቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ በነበሩበት ወቅት ሲሆን፣ እነዚህ ሁለት ሴቶች ለቻፕተሩ ምስረታ እውን መሆን የነበራቸው አበርክቶ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነበር። ድርጅቱ ሥራውን የጀመረውም፣ የትምህርት ሚኒስቴር ባመቻቸው ቢሮ ውስጥ ነው። ነገር ግን፣ የቻፕተሩ እንቅስቃሴ ከአንድ ዓመት በኋላ እያደገ እና እየሰፋ በመምጣቱ፣ ተግባራቱም በአይነትም እየበዙ ስለመጡ፣ በትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠው ይህ ፅህፈት ቤት ግን ይህን ለውጥ ለማስተናገድ በቂ አልነበረም።

በመሆኑም፣ ቻፕተሩ ፕሮግራሞቹን እና ፕሮጀክቶቹን ለማስኬድ ምቹ ወደሆኑት ቢሮዎች በመዛወርም፣ በአዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ቢሮዎችን በመከራየት ተንቀሳቅሷል። በዚህ ረገድ፣ ቦሌ መንገድ በሚገኘው ሜጋ ህንጻ ውስጥ ተከራይቶት የነበረውን ቢሮ አስታውሳለሁ ቻፕተሩ በዚህ መልኩ ለዓመታት በከተማዋ ወደ ሚገኙ የተለያዩ ሥፍራዎች ውስጥ ከተዘዋወረ በኋላ፣ በአሁኑ ወቅት መገናኛ አያት መንገድ ጉርድሾላ አካባቢ በሚገኘው በራሱ ቢሮ ውስጥ ተግባሩን በማከናወን ላይ የሚገኝበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ቀደም ብዬ እንደጠቀምኩት፣ ከምስረታው ጊዜ አንስቶ ቻፕተሩ ያደረገው ይህ መሰሉ እድገቱ እና ለውጡ፣ ቻፕተሩ በከፍተኛ ስኬታማ ጉዞ ውስጥ መሆኑን ለመመስከር የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፣ የቻፕተሩንም ሥራ በዘላቂነት ለማስቀጠል እና በልጃገረዶች ትምህርት ላይ ያለውንም ተፅእኖ የበለጠ ለማጉላት በሚደረገው ጉዞ ውስጥ አይነተኛ ድርሻ ይኖረዋል።

ትማር፡- ፋዌ ኢትዮጵያ፣ በሴቶች ትምህርት ዙሪያ እና ሴቶችን በማብቃት ረገድ እያካሄዳቸው ባሉ ተግባራቱ አንባር ከሌሎች ድርጅቶች የሚለየው በምንድን ነው?

እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፡- ፋዌ ኢትዮጵያ፣ የሴት ልጆችን አቅም በማሳደግ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ ድርጅቶች፣ በፕሮግራሞቹና በፕሮጀክቶቹ የአተገባባር ሂደት ውስጥ ሁሉን አቀፍ የሆነ የትግበራ ስልትን የሚጠቀም በመሆኑ ይለያል ማለት እንችላለን። በጥናት እና ምርምር ላይ ተመስርቶ በሚተገብረው በዚህ የትግበራ ስልቱ መሰረት፣ በፕሮግራሙ ለታቀፉ ሴት ልጆች ኢኮኖሚያዊ እና የፋይናንስ ድጋፍ ከማድረግ ጎን ለጎን፣ የልጃገረዶችን ግላዊ ሰብእናቸውን የሚያዳብሩ አቅማቸውንም የሚያንጸባርቁ ተግባራትን በማስፋፋት፣ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የመማር ማስተማር ዘይዎችን በመተግበር እና ትምህርትን በፍትሃዊነት፣ በአኩልነት እና በፍትሃዊነትን ተደራሽ በማድረግ ላይ ያተኮሩ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን በመደገፍ ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ተግራትን ያከናውናል።

ቀድም ብዬ እንደጠቀስኩት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር፣ ሴት ልጆችን በማብቃት ረገድ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ እና የፋይናንስ የድጋፍ ውጥኖችን ከመተግበሩ በተጨማሪ፣ ፕሮጀክቶቹን መሰረት በማድረግ በሚተገበሩ የተለያዩ ተግባራት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ያደርጋል። ከዚህ አኳያ ከሚጠቀሱ እና ሥራ ላይም ካዋላቸው የተነሳሽነት ፕሮግራሞቹ እና ፕሮጀክቶቹ መካከል አንዱ፣ በስዋሂሊ "እንናገር" የሚል ትርጉም ያለው የቱስሜ (TUSEME) ፕሮግራም ነው። ይህ ፕሮግራም፣ ራስን ወደ ውስጥ የመመልከት እና ስሜታዊ ምላሾችን እና ባህሪያትን የመመርመር ሂደትን በማጎልበት፣ ልጃገረዶች ስለማንነታቸው ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይረዳል። ይህ የተነሳሽነት ፕሮግራም፣ ለሴት ልጆችም ብቻ ሳይሆን፣ በፕሮግራሙ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ ላላቸውም ጭምር ጠቃሚነት ያለው ነው።

ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው ተግባራት በተጨማሪ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ የተለያዩ ፖሊሲዎች ሥርዓተያታን ያማከሉ እንዲሆኑ የሚያስችሉ በፖሊሲ ለውጥና ግንዛቤ ማሳደግ ላይ ያተኮሩ ተግባራትን ያከናውናል። እንዲሁም፣ በማናቸውም ተግባራት ውስጥ የወንዶችን እና የሴቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በማስፈን እና ልጃገረዶች በማናቸውም የትምህርት ደረጃዎች ውስጥም በእኩልነትና በፍትሃዊነት ተሳትፈው ትምህርታቸውን በውጤታማነት

እንዲያጠናቅቁ የሚያስችሉ ተግባራትንም ጨምሮ ያካሂዳል። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሰረት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ የሚያከናውናቸው የፖሊሲ ለውጥን እና ግንዛቤን ማሳደግ ላይ በማተኮር የሚያከናውናቸው ተግባራቱ በጥናትና ምርምር የተደገፉ እንዲሆኑ ያደርጋል። እነዚህ ጥናትና ምርምሮቹ፣ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት በቂ እውቀትና ግንዛቤ እንዲኖረው ከማስቻላቸው በተጨማሪም፣ ሴት ልጆች በሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶችም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከወቅቱ ጋር የተገናዘቡ መረጃዎች እንዲኖሩት ያስችላሉ፤ በግኝቶቻቸው ላይ በመመስረትም ለውጤት የሚያበቁ ተግባራትን በመቅረፅ ሥራ ላይ እንዲያውልም ያግዛሉ። ባጠቃላይ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ በእነዚህና በሌሎች ውጤታማ ተግባራቱ አማካይነት በልጃገረዶች ትምህርት ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው ብዬአምናለሁ።

ትግር፡- የፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት (FAWE RS) የቦርድ አባል እንደመሆኖም፣ አህጉራዊው ጽ/ቤት በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታን ፍትሃዊነትን እና እኩልነትን የማስፈን ተልእኮውን ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ለማሳካት የሚያደርገውን አስተዋፅኦ እንዴት ይገልጹታል?

እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፡- የፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት (FAWE RS) ከተለያዩ አጋሮቹ ጋር በትብብር ይሠራል። በተለይም፣ ጽ/ቤት በአፍሪካ ህብረት (AU) ውስጥ መቀመጫ እንዲኖረው በመደረጉ፣ በህብረቱ ውስጥ የተለያዩ ኮሚቴዎችን በጥምረት በመምራት ተሳትፎ እያደረገ ሲሆን፣ የሴቶችን ትምህርት የሚመለከቱ የተለያዩ ጉዳዮች በዚህ አህጉራ ዊድርጅት በኩል ትኩረት እንዲያገኙ ትልቅ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል።

የፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት ይህንን እና ሌሎች ትስስሮቹን በመጠቀም፣ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፉ በርካታ ዝግጅቶችን እና ኮንፈረንሶችን በተሳካ ሁኔታ በማዘጋጀት፣ በሴቶች ትምህርት ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ ለመፍጠር የታለሙ የግንኙነት እድሎችን ማስፋትችሏል። በአጠቃላይም፣ ፋዌ ከሴቶች ትምህርት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚቀረፁ የተለያዩ የፖሊሲ አቅጣጫዎች አንፃር የተሟጋችነት ሚናውን በመጫወት፣ ጥናትና ምርምር በማካሄድ፣ ስለሴቶች የትምህርት ተሳትፎ እድገት እና ትምህርታቸውንም በውጤታማነት ማጠናቀቅ ስለሚችሉበት ሁኔታ መከናወን ባለባቸው ተግባራት እና በሌሎች ተያያዥ ጥረቶች አንፃር በትኩረት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

የፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት፣ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት በሚገኙ 34 ብሄራዊ ቻፕተሮች በኩል ተግባራቱን ያከናውናል። እነዚህ ቻፕተሮች፣ ተግባራቶቻቸውን ከአህጉራዊው ጽ/ቤት ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ስትራቴጂያዊ እቅዶች ጋር በማገናዘብ ይተገብራሉ። ስለዚህ፣ ቻፕተሮቹ እየተገበሯቸው ያሉ እቅዶቻቸውም ሆኑ ተግባሮቻቸው በመላከፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት ስትራቴጂያዊ ማዕቀፍ ጋር የተሰናሰሉናቸው።

የፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት፣ 34 ቱቻፕተሮች ለተለያዩ እቅዶቻቸውና ተግባራቶቻቸው፣ በተለይም ለምርምር ፕሮጀክቶቻቸው ዳር መድረስ አስፈላጊየሆኑ የሀብት ምንጮችን እንዲያገኙ የሚያስችሉ ትስስሮችን እንዲፈጥሩ በመደገፍ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል። በተጨማሪም፣ ጽ/ቤቱ እነዚህ ቻፕተሮች የየራሳቸውን የትግበራ ስልቶች እንዲቀርጹ እና በየሀገራቸውም እያሳደሩት ያለውን ተፅእኖ ይበልጥ እንዲያጎለብቱ ያበረታታል።

ትግር፡- በአገራችን የአጠቃላይ ትምህርት በተለይም በሴት ልጆች የትምህርት ተሳትፎ እና በፆታ እኩልነት ዙሪያ ፋዌ ኢትዮጵያ እያደረገ ያለውን አስተዋፅኦ እንዴት ይገመግሙታል?

እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፡- ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር፣ ከተልዕኮው፣ ከግቡ እና ከዓላማው ጋር በተጣጣመ መልኩ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በጋራ ይሠራል። በዚህ ረገድ በዋናነት የሚተቀሰው ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ነው። ማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ ለበርካታ ዓመታት የቻፕተሩን በርካታ የስኮላርሺፕ መርሃግብሮችን በገንዘብ ሲደግፍ ቆይቷል፤ ይህ ድጋፉም እየቀጠለ ይገኛል። ከፋውንዴሽኑ የተገኘው ይህ የገንዘብ ድጋፍ፣ ተሰጥኦ ያላቸው እና ልዩልዩ ወጣት ግለሰቦች፣ በተለይም ወጣት ሴቶች የመሪነት ቦታ እንዲይዙ፣ ምኞታቸውን እንዲያሳኩ እና ለማህበረሰባቸውም ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በማስቻል ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በተጨማሪም፣ ይኸው ድጋፍ በፋዌ ኢትዮጵያ በኩል የሚከናወኑ የተለያዩ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን በመደገፍ ረገድም አስተዋፅኦም ነበረው።

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ለሴቶች ትምህርት መሻሻል፣ ለተሳትፏቸው ማደግ እና ለአጠቃላይ ስኬቶቻቸው መጎልበት በሚያደርገው ጥረት ውስጥ፣ እንደ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ሁሉ በርካታ ድርጅቶችም ከፋዌ ኢትዮጵያ ጎን በመሆን በአጋርነት እየተሳተፉ ይገኛሉ። በዚህም መሰረት፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሴት ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅ፣ በተለያዩ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በመከታተል ከእነዚህ ተቋማት ተመርቀው የግል ህይወታቸውን መምራት ጀምረዋል። ከዚህ በተጨማሪም፣ በፋዌ ኢትዮጵያ የተለያዩ መሰል ድጋፎች በተተገበሩ የተለያዩ ፕሮግራሞቹ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ የቀድሞ ተጠቃሚዎች፣ በሴቶች ትምህርት መሻሻል ዙሪያ ግንዛቤን በማሳደግና በልዩልዩ ተዛማጅ ተግባራት ውስጥም በበኩላቸው እያደረጉት ያለው የነቃ ተሳትፎ ለተግባራቱ ውጤታማነት እንደማሳያ ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው። እንዲሁም፣ በስኬት የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ለራሳቸው እና ለቤተሰባቸው ህይወት መሻሻል የሚኖራቸውን ድርሻ በመረዳት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ በፕሮግራሙ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ሴቶች በአነስተኛ የንግድ ሥራ እንዲሰማሩ ምየበኩሉን እገዛ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል።

ትግር፡- በመጨረሻም፣በእስካሁኑ ጉዞው ያስመዘገባቸውን ውጤቶቹን መሰረት በማድረግ፣ ስለ ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ከንውንም ሆነ በቀጣይነትም ሊያከናውናቸው ይገባሉ ስለሚሏቸው ጉዳዮች ማጋራት የሚፈልጓቸው ጉዳዮች ካሉ ቢጠቅሰሉን?

እመቤት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፡- ለልጃገረዶችና ባጠቃላይም ለሴቶች ትምህርት የሚሰጥ ትኩረት፣ በየትኛውም አገር የእድገት ጥረት ውስጥ ወሳኝነት ያለው ጉዳይነው። ይህም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው እውነትነቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ለልጃገረዶች የትምህርት እድል መስጠት የሚያስገኘው ጥቅም መሰረት ያለው ለመሆኑ ሰበቡ፣ ትምህርት ነፃነታቸውን የሚያጎለብቱበትን ስብእና የሚያዳብርላቸው ከመሆኑ በተጨማሪ፣ የራሳቸውን ቤተሰብ እንዲያስተምሩ እና የወደፊት ትውልድንም ለመቅረፅ በሚኖራቸው አስተዋፅኦ ረገድ የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ መሆኑ ነው።

በተጨማሪም፣ የተማሩ ሴቶች በእያንዳንዱ ሃገር ኢኮኖሚያዊ የእድገት ጉዞ ውስጥ የሚኖራቸው ተፅእኖእና ለውጤታማነቱ ያላቸው አስተዋፅኦ የሚጠያይቅ አይደለም። ይህንን እውነታ በመረዳት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ የበርካታ ልጃገረዶችን የትምህርት ስኬት በማሳደግ ረገድጉልህ የሆነ ድርሻውን ተወጥቷል ማለት ይቻላል። ሆኖም፣ ከዚህ ስኬታማ ጉዞ ጋር በተያያዘ፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሴት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመጡ የሚያደርጉ፣ ትምህርታቸውንም በሚገባ እንዳይከታተሉ እናውጤታማ ሆነውም እንዳያጠናቅቁ የሚከለክሉ መሰናክሎች አሁንም እንዳሉባቸው መረዳት ተገቢ ይሆናል።

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ በሴቶች ትምህርት ዙሪያ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራትን ማስቀጠል እንዲችል፣ የተለያዩ ሃሳቦችን ማመንጨት እና የፖሊሲ አማራጭ ሃሳቦችን ማቅረብ የሚችልባቸውን ጥናት እና ምርምሮችን ማካሄድ እንዲችል፣ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር እየፈጠረ ያለውን ግንኙነት ይበልጥ አጠናክሮ መቀጠል አለበት። ከዚህ በተጨማሪም፣ የሴቶች ትምህርት የልማት ወሳኝ ገጽታ ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ የሰብአዊ መብት ጉዳይ እንደመሆኑ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ የምስረታው ዋና ምሰሶ በሆነው እና በሴቶችትምህርት ዙሪያ በተለያየ መልኩ እያካሄደ ባለው የተሟጋችነት ተግባሩ ጠንክሮ መጓዝ ይኖርበታል።



የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ

ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር፣ 32 ተሳታፊዎች በተገኙበት በአዲስ አበባ በሚገኘው ቶፕ ቴን ሆቴል አመታዊ ጠቅላላ ጉባዔውን መጋቢት23 ቀን2024 ዓ.ም. አካሂደዉ። በዚህ ጉባኤ ላይ፣ ቻፕተሩ እ.ኤ.አ. በ2023 ዓ.ም. ዓመታዊ እቅዱ መሰረት ያከናወናቸው ተግባራትና አፈፃፀማቸው ቀርበው ሰፊ ውይይት እና ግምገማ ተካሂዶባቸዋል። እንዲሁም፣ በጉባኤው የ2023 ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። በጉባኤው ላይ የፋዌ ኢትዮጵያ ቦርድ አባላት፣ የንዑስ ቻፕተሮች ተወካዮች፣ ከአጋር ድርጅቶች እና ከተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የተውጣጡ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተሳትፈዋል።

በጠቅላላ ጉባኤው ፕሮግራም መሰረት፣ የፋዌ ኢትዮጵያ ቦርድሰብሳቢ የሆኑት ወ/ሮአልማዝወ/ተንሳይ፣ የቦርዱን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለጉባኤው አቅርበዋል። ወ/ሮ አልማዝ ወ/ተንሳይ፣ በዚሁ ሪፖርታቸው፣ ፋዌኢትዮጵያ በዓመቱ እቅድ መሰረት በርካታ ተግባራት በቦርዱ የቅርብ ክትትል ያከናወነ መሆኑን በመረጃ አስደግፈው ያቀረቡ ሲሆን፣ በተለይም የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ በማጎልበት እና በትምህርት ዘርፍ ውስጥ ያሉ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነቶችን በመቅረፍ ረገድ የተከናወኑ ተግባራት ስለነበራቸው ጉልህ አስተዋፅዖ፣ የተለያዩ የስኬት መረጃዎችን በማስደገፍ ገልፀዋል። እነዚህ ተግባራትም፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግስት በኩል እየተተገበሩ ካሉ ሥርዓተ ፆታን መሰረት ካደረጉ የትምህርት ተነሳሽነቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ወ/ሮ አልማዝ በዚሁ ሪፖርታቸው አመልክተዋል።

ወ/ሮ አልማዝ ወ/ተንሳይ የፋዌ ቦርድን ዓመታዊ ሪፖርት ካቀረቡ በኋላ፣ የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት ወ/ሮሰላማዊት አድማሱ፣ በፋዌ ኢትዮጵያ ጽህፈትቤት ክትትልና ቁጥጥር እ.ኤ.አ. በ2023 ዓመታዊ የእንቅስቃሴ እቅድ መሰረት በተለያዩ የቻፕተሩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች አማካይነት የተከናወኑ ተግባራትን በዝርዝር ያመለከተ የአፈፃፀም ሪፖርት አቅርበዋል። ወ/ሮ ሰላማዊት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ በእነዚህ የቻፕተሩ የተለያዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች በኩል የተከናወኑ ተግባራት በተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም በተለያዩ የድጋፍ አማራጮች ተደግፈው የተተገበሩ መሆናቸውን ጠቁመው፣ በቻፕተሩ ዓመታዊ እቅድ መሰረትም ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠናቀቃቸውን አስገንዝበዋል። ከወ/ሮ ሰላማዊት የሥራአፈጻጸም ሪፖርት በኋላ፣ የጠቅላላ ጉባኤው ተሳታፊዎች በቦርዱ ሰብሳቢ እና በቻፕተሩ ሥራ አስፈፃሚ በቀረቡ ሪፖርቶች ዙሪት ላይ ጥልቅ ውይይት አካሂደዋል። በመቀጠልም፣ ለጉባዔው በተዘጋጀው መርሃግብር መሰረት፣ የፋዌ ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተሮች ተወካዮች፣ የየቻፕተራቸውን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በዓመታዊ እቅዳቸው መሰረት አቅርበዋል፤ የጉባኤው ተሳታፊዎችም በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ሰፊ ውይይት አድርገዋል።

በዓመቱ ጉባኤ ማጠቃለያ ላይ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ አሁን ለደረሰበት ደረጃ እንዲበቃ በምስረታው ሂደት ከፍተኛ ድርሻ ለነበራቸው መስራች አባላት ዕውቅና የተሰጠበት ሥነሥርዓት የተካሄደ ሲሆን፣ በዚሁ ሥነስርዓት ላይ የተከበሩ አምባሳደር ገነትዘውዴ (ዶ/ር) በዚህ ረገድ ለነበራቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ግምት በመስጠትም የድርጅቱ የክብር አባልነት ክብር ተጎናፅፈዋል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ፋዌ ኢትዮጵያን ለበርካታ ዓመታት በዋና ሥራ አስፈፃሚነት ሲያገለግሉ ለቆዩት ለወ/ሮ ሮማን ደገፋ ለነበራቸው አበርክቶ እውቅና የሰጠ ይፋዊ የስንብት ሥነስርዓትም በዚሁ ወቅት ተካሂዷል። በጠቅላላ ጉባኤው ማጠናቀቂያ ወቅት ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ሌላው፣ የአካዳሚክ ባለሙያዎች፣ አስተማሪዎች፣ የሥርዓተ-ፆታ ተሟጋቾች እና በተለያዩ በጎ ተግባራት ውስጥ የመሳተፍ ፍላጎቱ ላላቸው ወጣቶች፣ በአጠቃላይም ለ18 አዳዲስ አባላት ለፋዌ ኢትዮጵያ በተለያየ መልኩ ስለሚኖራቸው አበርክቶ እና ተሳትፎ ግንዛቤ መፍጠር ላይ ያተኮረ የትውውቅ መድረክ ተከናውኗል።

ሴፕቴምበር 24፣2024 ዓ.ም.

ለአፍሪካ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ቁልፉ ሴት ልጆችን ማስተማር ነው

በሪታ ሮይ ፣ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሬዝዳንት እና ዋና ሥራ አስፈፃሚ

የአፍሪካ ሴቶች አምቅ ኢኮኖሚ አቅሞቻቸውን ወደተግባር መለወጥ የሚያስችሏቸውን አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር፣ እ.ኤ.አ. በ2030 ላይ በአፍሪካ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ላይ ተጨማሪ የ287 ቢሊዮን ዶላር ሃብት መጨመር እና ለ23 ሚሊዮን አዳዲስ የሥራ እድሎች መፈጠር ድርሻ እንደሚኖረው የተተነበየ ቢሆንም፣ ዛሬ ላይ ግን ከዚህ ትንበያ በተቃራኒው 28 በመቶ የሚሆኑ ወጣት ሴቶች ብቻ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቅቃሉ። ማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ በሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ረገድ በተጨባጭ እየተስተዋለ ያለውን ይህን ችግር ለመቅረፍ፣የሴት ልጆች የትምህርት ተደራሽነት እንዲሰፋ እና በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸው ቆይታም እንዲሻሻል የሚያስችሉ ተግባራትን በየሃገሩ ካሉ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በትብብር በማከናወን ላይ ይገኛል።

በአዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦቻቸው እና በሥራ ፈጠራ ረገድም እየታዩባቸው ባሉ ተነሳሽነቶች የተነሳ፣ የአፍሪካ ወጣቶች በአህጉራቸው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገቶች ውስጥ ሁነኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት ከአህጉሩ ጠቅላላ ህዝብ ውስጥ 40% የሚሆነው ከ15 አመት በታች በሆነበት እና በ2050 ዓ.ም. ላይም ሌሎች 100 ሚሊዮን ልጆች አህጉሩን እንደሚቀላቀሉ በተገመተበት ሁኔታ፣ አፍሪካ በዓለምአቀፍ ደረጃ በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰፊ የሥራ ሃይል በ2035 ዓ.ም. ላይ እንደሚኖራት ተገምቷል።

ይህም፣ በአህጉሪቱም ሆነ በዓለም ደረጃ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ጤናን በማሻሻል፣ ዓለማችንንም ከተለያዩ አሉታዊ ጉዳዮች በመታደግ እና አዳዲስ የሥራ እድሎችን በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ነገርግን፣ ይህን የወጣቱን ትውልድ አስተዋፅዖ በሚገባ መጠቀም እንዲቻል፣ አንድ ቁልፍ ጉዳይ የተለ የትኩረትን የሚሻ እንደመሆኑ፣ በመላው አፍሪካ ያሉ ወጣት ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ሙሉ አቅምን እና ልዩችሎታን አሟጦ በመጠቀም ረገድ በተለየ መልኩ በትኩረት መንቀሳቀስ ይገባል።

የማስተርካርድ ፋውንዴሽን አማካይነት በተዘጋጀውና "ወጣት ሴቶች በአፍሪካ፣ የ2030 ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ለውጥ ተዋናዮች" በሚል ርእስ ይፋ በተደረገው አዲስ ዘገባ እንደተገለፀውና ቀደም ብሎም እንደተጠቆመው፣ የወጣት ሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ምርታማነትን በማፋጠን ብቻ፣ በአፍሪካ 287 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ኢኮኖሚያዊ ሀብትን መፍጠር ይቻላል። ይህ ወደ ኢኮኖሚው የሚገባው ሃብትም፣ በጠቅላላው የሀገርውስጥ ምርት ላይም የ5 ከመቶ እድገት እንዲኖር የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ለ23 ሚሊዮን የአህጉሪቱ ዜጎችም የሥራ እድልን መፍጠር ያስችላል።

ይህንን ለማሳካት ግን፣ በርካታ አዎንታዊ ግባራት እንዲከናወኑ ይጠበቃል። በዚህም መሰረትም፣ በዋናነት በልጃገረዶች እና በወጣት ሴቶች የትምህርት ተደራሽነት ላይ እና በትምህርት ቤትም እንደቆዩ በሚያስችሉ ተግባራት ላይ በተለየ ትኩረት መንቀሳቀስ ይገባል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ በአሁኑ ወቅት፣ እድሜያቸው ለሁለተኛ ደረጃ ከደረሱ የአፍሪካ ወጣት ሴቶች መካከል፣ 34 ሚሊዮን የሚሆኑት በትምህርት ገበታ ላይ አይገኙም። እንዲሁም፣ ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሃገራት ውስጥ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ ወጣት ሴቶች መካከል ትምህርታውን እስከ መጨረሻው በመግፋት የሚያጠናቅቁት 26 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም፣ የሁለተኛ ደረጃት ምህርታቸውን ተከታትለው ከሚጨርሱት ከእነዚህ ሴት ተማሪዎች መካከል ደግሞ፣ የከፍተኛ ትምህርት መከታተል የሚያስችላቸውን ውጤት እያስመዘገቡ የሚገኙት 8% ያህሉ ብቻ ናቸው። ከዚህ በላይ በአፍሪካ የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ረገድ የቀረቡ መረጃዎች፣ በግለሰብ ደረጃ በሚመዘገብ የህይወት ዘመን ምርታማነት እና ገቢ ላይ የሚኖራቸው አሉታዊ ጫና፣ በአህጉር ደረጃ እንዲመዘገብ ከሚጠበቀው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት እስከ 10 ቢሊዮን ዶላር ከሚደርስ ኪሳራ ጋር የሚስተካከል እንደሆነ ያጠቀሳል።

ማስተርካርድ ፋውንዴሽን እንቅስቃሴ መሰረቱ፣ ለሁሉ ምሰው የመማር እና የመበልፀግ እድል የምትሰጥ ዓለምን እውን ማድረግ የሚለው ራእይ ነው። በዚህም መሰረት፣ ፋውንዴሽኑ የልጃገረዶችን ትምህርት በመደገፍ እና የሴቶችን የሥራ ሃይል ተሳትፎ በማሳደግ ዙሪያ ሁነኛ ሚና እየተጫወቱካሉ የተለያዩ ድርጅቶች ጋርእጅና ጓንትበመሆን ባለፉትአስርት ዓመታትበርካታ ተግባራትን በትብብር ሲያከናውን ቆይቷል። ለእነዚህ አጋሮቻችን ቁርጠኝነት እና የየአካባቢዎቻቸውንም ችግሮች ከመሰረቱ ለመፍታት ለሚያደርጉት ያላሳለሰ ጥረት ምስጋና ይግባውና፣ ራእያችንን ዕውን በማድረግ በኩል ከፍተኛ እድገት እና ለውጥ ታይቷል፤ እየታየም ይገኛል።

እስካሁን ድረስ፣ በተለያዩ ሃገራት ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ከ40 በላይ አጋር ድርጅቶች በትብብር በተከናወነው የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የስኮላርሽፕ ፕሮግራም አማካይነት፣ ከ45,000 በላይ ወጣት ሴቶች እና ወንዶች ዋራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ እና የአመራር አቅማቸውንም ማዳበር የቻሉባቸው በርካታ ተግባራት ሊከናወኑ ችለዋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ቴክኖሎጂ ዋራት ያለው ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ ረገድያለውን አስተዋፅኦ በመገንዘብ፣ ከተለያዩ ወጣት የኤድቴክሥራ ፈጣሪዎች(EdTech Entrepreneurs) ጋርባለን ትብብር አማካይነት ዋራቱን የጠበቀ ትምህርት በተለያዩ ዲጂታል አማራጮች ተደራሽ እንዲሆን የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራት ሥራ ላይ ውለዋል። በዚህ ምስልት፣ 2 ሚሊዮንያህል ወጣቶችን ተደራሽ ማድረግ የተልናከናውናቸው የሚገቡ በርካታሥራዎች ከፊታችን አሉ

በፋውንዴሽናችን ራዕይ መሰረት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ተደራሽነት በማስፋት እናየድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የተለያዩ አማራጮችን፣ ማለትም፣ የከፍተኛ ትምህርትን፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን እና የተለያዩ የሥራ እድሎችን ፈጣሪየሆኑና በእስካሁኑ ሂደትም ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመተግበር ላይ እንገኛለን። እነዚህ ፕሮግራሞቻችን፣ ለልጃገረዶች እና ለወጣት ሴቶች የትምህርት ተደራሽነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፤ ትምህርታቸውንም በሚገባ እንዲያጠናቅቁ እገዛ ያደርጋሉ።

በሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት፣ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ ከ70,400 በላይ ወጣት ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ለመደገፍ፣ የሴቶች ትምህርት ዘመቻ (CAMFED) እና የአፍሪካ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች መድረክ (FAWE) ከተሰኙት አጋር መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የፈጠረውን የረጅም ጊዜ ትብብር በከፍተኛ ሁኔታ በማስፋት የመንቀሳቀስ ትልሙን እውን ያደርጋል። ይህ የ360 ሚሊዮን ዶላር በጀት የተያዘለት ፕሮግራም በዋናነት ትኩረት ያደረገው፣ የኢኮኖሚ ተግዳሮት ካሉባቸው ማህበረሰቦች የተገኙ 70,400 ሴቶችን እና ልጃገረዶች ላይ ነው። በዚህ ፕሮግራም አማካይነትም፣ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ትምህርታቸውን ባግባቡ እንዲጨርሱ፣ የራሳቸውንም ንግድ እንዲያንቀሳቅሱ፣አሊያም ራሳቸውን ለሥራው ዓለም ዝግጁ የሚያደርጉባቸው የተለያዩ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይጠበቃል።

በማስተርካርድ ፋውንዴሽን አማካይነት በተተገበሩ ፕሮግራሞች በኩል፣ በእስካሁኑ ሂደት በርካታ ልጃገረዶችና ሴቶች ተጠቃሚ በመሆን ስኬታማ ሆነዋል። ለዚህም በርካቶችን ምሳሌ ማድረግ የሚቻል ሲሆን፣ ለዚህ ጽሁፍ ግን ጁሊያናን እንደ ምሳሌ እንውሰድ፣ በጋና ሰሜናዊ ምሥራቅ ክልል ከሰባት ቤተሰብ የተወለደችው ጁሊያና ብቁ ነርስ ለመሆን ያደረገችው ጉዞ በብዙ መልኩፈታኝ ነበር። ወላጆቿ አርሶ አደር እንደመሆናቸው፣ ጁሊያና የትምህርት ቤት ክፍያዋን ለመፈፀምም ሆነ የትምህርት ቁሳቁስ ለማሟላት በብዙ ተቸግራ ትምህርቷን ባግባቡ ለመከታተል ስትችገር ቆይታለች። ሆኖም፣ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን፣ ከሴቶች ትምህርት ዘመቻ (CAMFED) ከተሰኘው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በነበረው ትብብር ባገኘችው የስኮላርሽፕ እድል አማካይነት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በሚገባ ማጠናቀቅ በመቻሏ፣ በጋና ሴንትራል ዩኒቨርሲቲ በነርስነት ትምህርቷን ማጠናቀቅ ችላለች።

ጁሊያና፣ ዛሬ ማህበረሰቧን በነርስነት በማገልገል ላይ የምትገኝ ሆናለች። ከዚህ ሥራዋ ጎንለጎንም፣ በምትኖርበት አካባቢ ማህበራዊእና አካባቢያዊች ግሮችን መሰረትያደረገና ከ100 በላይአሚሆኑ ሴቶችየሥራ እድልእየሰጠ የሚገኘውንና "የሱምዋናየሺዓ ቅቤ ማቀነባበሪያ እና ግብይት የህብረት ሥራ ማህበር" የተሰኘን የንግድ ድርጅት በአመራርነት እየመራች ትገኛለች። ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው የጁሊያና ስኬቶች፣ ለትምህርት ተደራሽነት እና ለሌሎች መሰል ተግባራት በተለያየ መልኩ የሚደረጉ ድጋፎች፣ የብዙዎችን ሴቶች ህይወት በመለወጥና ማህበረሰብን በማሻሻልረገድ ሁነኛሚና እንደሚጫወቱ አይነተኛ ምስክር ናቸው።

ማስተርካርድፋውንዴሽን፣ በሴቶችልጆች ትምህርትዙሪያና እናወጣት ሴቶችንበማብቃት ላይከሚንቀሳቀሱት እናቀደም ብለንከጠቀስናቸው ከ"ዘመቻለሴቶች ትምህርት(CAMFED)" እናከ"አፍሪካሴት የትምህርትባለሙያዎች መድረክ(FAWE)" ከመሳሰሉአፍሪካ በቀልድርጅቶች ጋርባለው ትብብርበመታገዝ፣ ከ10 የአፍሪካሀገራት የትምህርትሚኒስቴር መስሪያቤቶች፣ ከ500 በላይዩኒቨርሲቲዎች እናየከፍተኛ ትምህርትተቋማት እናከ1,400 በላይከሆኑ የሁለተኛደረጃ ትምህርትቤቶች ጋርያለውን ትብብርይበልጥ አጠናክሮይቀጥላል። በዚህም፣በየሃገራቱም ሆኑየትምህርት ተቋማቱእየተተገበሩ ያሉየትምህርት ሥርዓቶች፣ለልጃገረዶችና ለወጣትሴቶች የተለያዩየትምህርት ፍላጎቶችምላሽ የሚሰጡእንዲሆኑ የበኩሉንድርሻ ይወጣል።

ፋውንዴሽናችን፣ በእነዚህ አጋር ድርጅቶች አማካይነት የገነባውን የትብብር ማዕቀፍ መሰረት በማድረግም፣ ከተለያዩ የመንግስት አካላት፣ ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በፈጠረው የትብብር መንፈስ አማካይነት፣ በወሊድ ምክንያት ትምህርታቸውን ለማቋረጥ የተገደዱ ወጣት ሴቶች ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ የሚያስችሉ አሠራሮች እንዲተገበሩ፣ ፍትሃዊ የሆነ የትምህርት በጀት አደላደል እንዲኖር እና የሚተገበሩ ፕሮግራሞች በስኬት እንዲጠናቀቁ የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል።

በአጠቃላይ፣ በተለያዩ የፋውንዴሽናችን እነዚህን መሰል ፕሮግራሞቻችን አማካይነት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለልጃገረዶች ተደራሽ እንዲሆኑ እና እነዚሁ ልጃገረዶችም ትምህርታቸውን በስኬት እንዲያጠናቅቁ የሚያስችሉ የተለያዩ የምክር አገልግሎቶች በትምህርት ቤቶች ለእነዚሁ ልጃገረዶች እንዲሰጡ ይደረጋሉ። በተጨማሪም፣ እነዚሁ ፕሮግራሞቻችን፣ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ወደከፍተኛ ትምህርት ለሚሸጋገሩ ልጃገረዶችም ቀጣይነት ያለው የድጋፍ ዕድሎችን ያመቻቻሉ። በእነዚህ ሥርዓት በተበጀላቸው የድጋፍ ፕሮግራሞቻችን አማካይነትም፣ በቀጣይ እስከ 3 ሚሊየን አካባቢ የሚደርሱ ወጣቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

የሴቶች ልዩ ሚና

ትምህርት፣ የአፍሪካን ኢኮኖሚያዊ እድገት እውን ለማድረግ እና ለማስቀጠል መሰረት ነው። በፋውንዴሽናችን የቅርብ ጊዜ ሪፖርት ላይ በዝርዝር እንደተገለፀው፣ የሴቶችን የሥራ ዓለም ተሳትፎ ለማሳደግና በስኬትም እንዲዘልቁ ለማስቻል፣ እንዲሁም የራሳቸውንም የሥራ ፈጥራ አንቀሳቃሽ እንዲሆኑ፣ ከትምህርት በተጨማሪ ለሌሎች ተግባራትም ትኩረት መስጠት ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ወጣት ሴቶች ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ማስኬጃ ካፒታልን፣ መሬትን፣ የሥራ መሣሪያዎችን የሚያገኙባቸውን ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ እንዲሁም የንግድ ትስስር እንዲፈጠሩ እና የገበያ እድሎችን እንዲያገኙ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ቀርፆ ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

እንዲሁም በዋናነት፣ ብዙ ሴቶች በቤተሰባቸው ውስጥ የሚጫወቱትን ልዩ ሚና በተለየ ሁኔታ መረዳት፣ ለዚህ ልዩ ሚናቸውም ተገቢውን ክብር መስጠት እና አስፈላጊውንም ድጋፍ እንዲያገኙ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። ለምሳሌ፣ ብዙ ወጣት እናቶች በተመጣጠኝ ዋጋ የልጆች እንክብካቤ አማራጮች እውን እንዲሆንላቸው፣ መንገዳገዶች እንዲመቻቹላቸው እና ፍላጎታቸውን ያማከለ የሥራ ሰዓት አጠቃቀም እንዲኖራቸው ይሻሉ። ለእነዚህና መሰል መሰረታዊ የወጣት እናቶች ፍላጎቶች መሟላት የሚሰጥ ትኩረት፣ ሴቶችን ከፍተኛ ክፍያ ወደሚያስገኙ ሥራዎች እንዲያዘነብሉ እና በአዳዲስ የሥራ ፈጠራ እድሎች ላይ በትኩረት እንዲንቀሳቀሱ አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር እንደመሆኑ፣ ለሃገራት አዳዲስ የሥራ ፈጠራ ክህሎቶች መዳበር እና ብዝሃነት ላይ ለተመሰረተ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴያቸውም የሚኖረው አስተዋፅኦ በጣም ከፍተኛ ነው።

የአፍሪካ ኢኮኖሚያዊ እድገት የወደፊት እጣ ፈንታ በወሳኝ ሁኔታ የተመሰረተው፣ በሁሉም የአህጉሪቷ ወጣቶች፣ በተለይም በልጃገረዶች እና በወጣት ሴቶች የተሟላ እና ትርጉም ያለው እንቅስቃሴ ላይ ነው። ስለሆነም፣ በመማር ማስተማር ውስጥ በሚከናወኑ ተግባራት በኩል፣ በሀገሮች መካካል በሚፈጠር ኢኮኖሚያዊ ውህደት እና በአስተሳሰብ ላይ በሚኖር ለውጥ አማካይነት፣ እያንዳንዷ ሴት ልጅ የምትማርበት እና ራሷን በራሷ በገቢዋ የምታስተዳድርበትን፣ ኑሮዋንም መምራትና ወደብልጽግና የምትንደረደርበትን መሰረት መጣል የሚቻልበትን የወደፊት ጊዜ መገንባት እንችላለን።

ይህ ራዕይ ብቻ አይደለም። ከራዕይ ባለፈ ሊታለፍ የማይገባ፣ ለበለፀገች እና ቀጣይነቷ በፅኑ መሰረት ላይ ለተጣለ አፍሪካ እውን መሆን የግድ መደረግ ያለበት፣ ሁላችንም እጅለእጅ ተያይዘን ልንተገብረው የሚገባ ጉዳይ ነው።

(ትርጉም በዝግጅት ክፍሉ።)

ጥቂት የምክር ቃላት.....

- ለመጸለይ ከፀሐይ ጋር ተነስ። ብቻህን ጸልይ። ብዙ ጊዜ ጸልይ። ብትናገር እግዚአብሔር ይሰማል።
- በመንገዳቸው የጠፉትን ታገስ። ድንቁርና፣ ትዕቢት፣ ቁጣ፣ ቅናት እና ስግብግብነት የሚመነጩት ከጠፋች ነፍስ ነው። ምሪትን እንዲያገኙ ጸልይ።
- ራስህን በራስህ ፈልግ። ሌሎች መንገድህን እንዲያበጁልህ አትፍቀድ። የአንተ መንገድ የአንተ መንገድ ብቻ ነው። ሌሎች አብረውህ ሊራመዱ ይችላሉ፤ ነገር ግን ማንም የአንተን መንገድ ሊሔድልህ አይችልም።
- ለእንግዳ ዋጋ ስጥ። በጣም ጥሩውን ምግብ አቅርብላቸው፤ ጥሩውን አልጋ ስጣቸው እና በአክብሮት ያዛቸው።
- ያንተ ያልሆነውን ከሰው፣ ከማህበረሰቡም ሆነ ከባህል አትውሰድ። ካላገኘህ ወይም ካልተሰጠህ ያንተ አይደለም።
- በዚህች ምድር ላይ የተቀመጡትን ነገሮች ሁሉ አክብር- ሰዎችም ይሁኑ ተክሎች።
- የሌሎችን ሃሳቦች፣ ምኞቶች እና ቃላት አክብር። ሲያወሩ በፍፁም አታቋርጥ፣ በጭራሽ አታላግጥ ወይም በስድብ አትመልስላቸው። የእያንዳንዱን ሰው እራሱን የመግለጥ መብት አትፈታተን።
- ስለ ሌሎች በመጥፎ መንገድ በጭራሽ አትናገር። ያወጣኸው አሉታዊ ኃይል ወደ አንተ ሲመለስ ይበዛል።
- ሁሉም ሰው ይሳሳታል። እና ሁሉም ስህተቶች ይቅር ሊባሉ ይችላሉ።
- መጥፎ አስተሳሰብ የአዕምሮ፣ የአካል እና የመንፈስ ህመም ያስከትላል። ብሩህ ተስፋን ተለማመድ። #የፍልስፍና ሀሁ፣ ፀሐፊ:~ ፖል ክሌንማን





የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የቀድሞ
ተማሪዎች የምስጋና ስነ ስርአት



የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር የቦርድ አባላት
ከክብርት አምባሳደር ዶክተር ገነት ዘውዴ

የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ንግግር



ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር አጋሮች

Ministry of Education

Ministry of Labor and Skill

Ministry of Health

Ministry of Women and Social Affairs

Regional Finance and Economic Development Bureaus

Regional State Educational Bureaus

Regional States Women, Children and Social Affairs Bureaus

Regional Labor and Skill

FAWE-Ethiopia's Sub-chapters

Mastercard Foundation/MCF

Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands

Urgent Action Fund Africa (UAF-Africa)

Plan International Ethiopia

Voluntary Service Overseas (VSO)

Young Men's Christian Association of Ethiopia (YMCA Ethiopia)

Ipas Ethiopia

Ethiopian Youth Federation

አዘጋጆች

ጌትነት ማሞ

ሃይማኖት ሙሉጌታ

ዲዛይነር

ማህደረ ተውልኝ



ትማር
TIMMAR

አሳታሚ፡
ፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር

+251 (0)11 667 6445
info@faweethiopia.org
www.faweethiopia.org
Salite Mihret, Sister Civil Society Organizations'
Common Office Building, 3rd floor